ግንቦት 2012 | ቅጽ 2

# ተልዕኮአችን



ራቪ ዘካርያስ
1946 – 2020

ነገር ግን ከህልሞች ሁሉ ታላቁ እግዚአብሔርን ማወቅ እና ለህወታችሁ ያሰበውን መረዳት ነው

**ልዩ ዘገባ**

## የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር

**በውስጥ ገጾች**

የእስልምናን አለም መረዳት

እንዴት በወንጌል እንድረሳቸው

የጸሎት ጥሪ ለሶማሌ ህዝብ ክፍል

# መልዕክት

ተልዕኮአችን የተሰኘው ይህ ዲጂታል መጽሔት አማኞችን በወንጌል ዙሪያ ለማስተማር እና ለማገዝ የተጀመረ ነው ። ይህ ዲጂታል መጽሔት ወንጌል እና ተልዕኮ ዙሪያ ላይ ብቻ ጽሁፎችን፣ ትምህርቶችን እና መልዕክቶችን የሚያቀርብ እንደሆነ አቀድሜ ለማሳወቅ እወዳለሁ። በመጽሐይቱ ላይ በሚጻፉ ጹሁፎች እንደምትጠቀሙ እና ዕውቀትን እንደምትገበዩበት ዕምነቴ ነው። ይህ መጽሔይት በየ15 ቀኑ ዲጅታል በሆኑ መንገዶች በቴልግራም እና ሌሎች የማህበራዊ ትስስር ገጻች የሚለቀቅ ሲሆን የምታገኙባቸውን ቻናሎች እንደሚከተለው እገልጻለው።

**Mission talk with Aman (https://t.me/NationsforGod)**
**Naoel's Perspective (https://t.me/NaolsP)**
**የቤሪያ ሰዎች በኢትዮጵያ (https://t.me/yeberiyasewoch)**

በየ አስራ አምስት ቀኑ በእነዚህ የቴልግራም ቻናሎች እና በተለያዩ የማህበራዊ ትስስር ገጻች ይለቀቃል። መልካም ንባብ እንዲሆንላቹ እመኛለው ።
በተጨማሪም ጥያቄ እና አስተያየት ካልዎት
በስልክ ቁጥር ፡- +251920293652/ +251940094767 ይደውሉ
ኢ-ሜይል ፡- trsionamanuel9@gmail.com
ያግኙን
አማኑኤል ገዛኸኝ

# ማውጫ


- እስልምናን መረዳት 1
- ታላቁ የወንጌል ጉዞ ፡ ራቪ ዘካሪያስ (1946-2020) 2
- ሙስሊሞችን በወንጌል የመድረሻ ስልቶች 4
- ክርስትና በቴህራን ምን ይመስላል 8
- የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር 11
- የጸሎት ጥሪ ለሶማሌ ህዝብ ክፍል 12
- የተልዕኮ መዘውር፡ ጀሽዋ ፕሮጀክት 14

# የእስልምናን አለም መረዳት

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 28፡ 19-20 በተለምደው የታላቁ ተልዕኮ ተብሎ የሚነገረው ክርስቶስ ለአማኞች እንድንፈጽመው የሰጠንን ተልዕኮ እናገኛለን። የወንጌሉ መልዕክተኝነት የቤት ስራም በክረስቶስ አማኖ የዳነ አማኝ ሁሉ ነው። ይህ ወንጌል ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚል የክርስቶስ ስም ባልተጠራበት ቦታ ሁሉ ሊነገር ለሰዎች ሁሉ አምላክ የሰጠውን የደህንነት መንገድ ልናበስር ግድ ይለናል።
ታዲያ ይህን የምስራች ወንጌል ላልደረሳት አለም ማበሰርን ስናስብ 1.7 ቢሊዬን ማህበረሰብ ያለውን የእስልምና አለም አለመረዳት እና ምንነት አለማወቅ የቤት ስራችንን ለመወጣት ተግዳሮት ከሚሆኑብን ነገሮች ግንባር ቀደሙ ነው። ዛሬ በአለማችን ወንጌል ያልደረሳቸው ህዝቦች ከሚከተሏቸው ሐይማኖቶች ሰፊውን ቁጥር የሚይዘው እስልምና ነው። ታዲያ አማኞች ይህ እውነት ላይ ተመርኩዘን በአካባቢያችን ያሉ ሙስሊሞችን ከመድረስ አልፎ እስከ አለም አቀፍ ንቅናቄ ድረስ ስናስብ ስለ እስልምና አጀማመር፣ የእስልምና አስተምህሮዎች እና ሌሎች ማወቅ የሚገቡን ቢያንስ መሰረታዊ እውነቶችን በዚህ ጽሑፍ ለመዳሰስ እሞክራለሁ። እስልምናን ለማወቅ በጣም ሰፊ ጥናት ይጠይቃል እንዲሁም በአንድ እና በሁለት ገፅ ሙሉ ምስሉን ለመስጠት ሊከብድ ይችላል ግን መሰረታዊ የተባሉትን ብቻ ለማንሳት እንሞክራለሁ።
እስልምና በሰባተኛው ክፍለዘመን መሐመድ በተባለ ሰው የተጀመረ ሐይማኖት ነው። ሙስሊሞች የቁርአኑን አስተምህሮ እና አምስቱን የእምነቱን አዕማድ ለመጠበቅ ይተጋሉ ።

## የእስልምና ታሪክ

በሰባተኛው ክፍለዘመን ላይ መሐመድ መልአኩ ገብርኤል እንደጎበኘው ይናገራል ። በዚህም እስከ መሐመድ መሞት ድረስ 23 ዓመታት በቆዬ መላዕክታዊ ጉብኝቶች የአላህን ( የአረብኛ ቃል ሲሆን አምላክን ለመግለጽ ይጠቀሙታል) ቃል "እንደገለጠለት" ይናገራል ። እነዚህ መገለጦች የእስልምናን ቅዱስ መጽሐፍ ቁርአንን ገንብተዋል። ኢስላም ማለት መማረክ ነው ይህ ቃል ሰላም ከሚል ስርወ ቃል የተወሰደ ነው። ሙስሊም ማለትም ለአላህ የተማረከ ማለት ነው።

## የእስልምና ህጎች

ሙስሊሞች አጠቃላይ ህጎቻቸውን በስድስት እምነቶች ላይ ይመሰርታሉ

1. በአንድ አምላክ እመን፡ ሙስሊሞች አላህ (አምላክ) አንድ እንደሆነ፣ ዘላለማዊ፣ ፈጣሪ እና ሉአላዊ እንደሆነ ያምናሉ
2. በመላዕክት ማመን
3. በነቢያት ማመን ፡ እነዚህ ነቢያት መጸሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትንም ነቢያት የሚጨምር ሲሆን ነገር ግን ሙሐመድን እንደ አላህ ( አምላክ) የመጨረሻ ነቢይ መቀበል
4. በአላህ መገለጥ ማመን፡ ሙስሊሞች የተወሰኑ የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ይቀበላሉ ይህም እንደ ህግ መጸሐፍት እና ወንጌላትን ነው። ቁርአኑ ዘላለማዊው የአላህ ቃል እንደሆነ ያምናሉ።
5. በመጨረሻው ቀን ፍርድ እና በቀጣዩ ማመን፡ እያንዳነዱ በትንሳኤ ቀን ህያውነትን ያገኛል ከዚያም ወይ ወደ ሰማይ ወይም ወደ ሲኦል ፍርድን ይቀበላል።
6.አስቀድሞ በተወሰነው ማመን፡ ሙስሊሞች አላህ (አምላክ) የሚሆነውን ሁሉ ወስኗል ። ሙስሊሞች ስለ አላህ (አምላክ) ሉአላዊነት ይመሰክራሉ" ኢንሻላህ" ( እንደ አላህ ፍቃድ) በማለትም ይህን ይመሰክራሉ

## አምስቱ የእስልምና ምሰሶዎች

እነዚህ አምስት መሰረታዊ መመሪያዎ ሊታዘዟቸው የሚገቡ መዋቅሮችን ያሳያሉ
1. የእምነት መግለጫ ( ሳሃዳ)፡ ላ ኢላ ኢላላህ ሙሀመድ ረሱል አላህ ፤ ይህም ማለት" ማንም የለም አላህ ብቻ፣ ሙሐድም የአላህ መልእክተኛ ነው። ማንኛውም ሰው ይህን የእምነት መግለጫ በመናገር ወደ እስልምና መቀየር ይችላል። ይህ የእምነት መግለጫ እንደሚያሳየው ሙስሊሞች አላህ ( አምላክ)
አንድ እንደሆነ ሙሃመድም አላህን (አምላክን) እንድገለጠው ያምናሉ
2. ጸሎት ( ሶላት) ፡ በየቀኑ አምስት የጸሎት ስርአቶች መተግበር አለባቸው
3. መስጠት ( ዛካት)፡ ይህ መስጠት በየአመቱ በሆነ መቶኛ ተሰልቶ የሚደረግ ነው
4. አጽዋዕማት ( ሳአወም) ፡ ሙስሊሞች በኢስልምና የግዜ ሰሌዳ በዘጠነኛው ወር የረመዳን ጾም ይጾማሉ። ጸሐይ እስክትጠልቅ ድረስ መብላትም ሆነ መጠጣት አይችሉም።
5. መንፈሳዊ ጉዞ (ሐጂ) ፡ የጤንነት እና የገንዘብ አቅም ካለ የሚደረግ ጉዞ ነው። ይህ የሃጂ ጉዞ በእስልምና የግዜ አቅጣጠር በ12 ወር ላይ የሚደረግ ነው።
የአንድ ሙስሊም ወደ ገነት የመግባት ሁኔታ የሚወሰነው ከላይ የጠቀስናቸውን አምስት የእምነት ምሰሶዎችን በመታዘዝ መተግበር ላይ የሚወሰን ነው ። ይህ ሁሉ አድርጎ ግን አላህ ( አምላክ) ብቁ ነው ብሎ ላያስብ ይችላል። በቁርአን ሱራ 46:9 እና በሐዲዝ 5.266 ላይ እንደተጻፈው ሙሐመድ እንኳ ወደ ገነት ያስገባው ይሆን አይሁን እርግጠኛ እንዳልሆነ ይናገራል።

ወደ ገጽ 3 ዞሯል ....

# ታላቁ የወንጌል ጉዞ
# ራቪ ዘካሪያስ (1946-2020)

ገና ህንድ ሀገር የኪርኬት ጨዋታ አፍቃሪ እያለ አንድ ቀን እናቱ ከነበረበት አስጠርታው በማህበረሰብ ውስጥ አለ የተባለ የመዳፍ አንባቢ ጋር አገናኘችው ፡ ሰውየውም የራቪን እጅ አንብቦ ነገውን ሊነግረው እጆቹን ስጠኝ ብሎ ጠየቀው። መዳፍ አንባቢው እጆቹን ትኩር ብሎ ከተመለከተ በኃላ ሟርት አይሉት ትንበያ እዚያ ትንሽ ልጅ ፊት ለእናቱ የንባቤ ውጤት ነው ያለውን ያወራት ጀመር ። እንዲህም አላት በህይወት ብዙ ርቀት አይጓዝም የእጆቹ መዳፍ ሚነግሩኝ ይህንን ነው ብሎ ተሰናብቷቸው ሄደ። የ37 ዓመቱ ራቪ ዘካሪያስ በወንጌላዊ ቢሊግራሃም ግብዣ አምስተርዳም ላይ የአለም አቀፍ ወንጌላውያን ኮንፍራንስ ላይ ሊሰብክ ተጠራ ። የክርስትና አቃቤ እምነት ለመሆን ወይም በእቅብተ ዕምነት አገልግሎት በብዙ ለመዘርጋት

እየጀመረ የነበረበት ወቅት ነበር። ከዚህ አንድ አመት በኃላ ራቪ ዘካርያስ ኢንተርናሽናል ሚስተሪስ የተባለ ተቋም መስርቶ "አሳቢውን አማኝ እና አማኙን አሳቢ መርዳት" በሚል አላማ ተነሳ።

የእጅ መዳፍ አንባቢው ነገውን በነገረው እና የራቪ ኢንተርናሽናል ሚኒስትሪስን በመሰረተበት አመታት መካከል ወደ ካናዳ ሄዶ ነበር፣ በሰሜን አሜሪካ ብዙ ቦታ በመዘዋወር ወንጌልን ይሰብክ ነበር፣ ቬትናም ለነበሩ የጦር እስረኞች በመጸለይ እና ካንቦዲያ የነበሩ ተማሪዎችን አገልግሎል እንዲሁም በግዜው ተመስርቶ ከነበረው ሚሲዬናዊያን አላያንስ ከተባለ አገልግሎት ጋር ባለቤቱን እና የመጀመሪያ ልጇን በመያዝ እየተዟዟረ አገልግሏል። ይህ ጉዞ አንግሊዝ ውስጥ የጀመረ፣ ሩቅ ምስራቅ እና በፓስፊክ ውቅያኖስ አውራጃ ላይ ባሉ ሃገራት የተጠናቀቀ አገልግሎት ነበር ። በነዚያ አመታት 600 የሚሆኑ መድረኮችን በብዙ ሃገራት እየተዞዞረ መስበክ ችሎ ነበር።

ራቪ ዘካሪያስ ደሊህ ሆስፒታል ውስጥ በ17 ዓመቱ ራሱን ለማጥፋት ሞክሮ የተረፈበት አጋጣሚ ተአምራዊም እና የህይወቱን አቅጣጫም የቀየረች ነበር። በዚያ ሆስፒታል በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ያለን የክርስቶስን ንግግር አነበብ እንዲህ ይል ነበር 9( እኔ ህያው ስለሆንኩ ህያዋን ትሆናላችሁ ይላል ለዚህም ቃል ምላሽ በመስጠት ራቪ ህይወቱን ለክርስቶስ አሳልፎ ሰጠ፤ አንድም ጸሎት ጸለየ «ከዚያ ሆስፒታል ድኜ ከወጣሁ እውነትን ፍለጋ የማልፈነቅለው ድንጋይ የለም» በማለት በፀሎቱ ለእግዛብሔር ቃል ገባ። የወንጌልን እውነት ካገኘ በኃላ ራቪ ለሌሎች ማጋራትየሚባለው እውነት ህይወቱን አሸነፈው እስከመጨረሻውም የሆነው ይህ ነው። የመዳን ተስፋው የመጨረሻ ደረጃ ላይ ሲደርስ የቀሩትን የመጨረሻ ቀናት ከቤሰቦቹ ጋር በቤቱ እንደያሳል ሲወሰን ኬሞቴራፒ ይከታተልበት ከነበረው የቴክሳስ ሆስፒታል ወደ ቤት ለመሄድ ሲወጣ ራቪ ዘካሪያስ ቤቱ የሚያደርሰው መኪናው ድረስ የተቀመጠበትን ጋሪ እየገፉ ለሸኙት ሶስት ነርሶች የክርስቶስን እውነት (ወንጌል) መስክሮላቸው ሰሰናበት ይህ ሰው በመጨረሻው እራሱ የማያቆ የምስክርነት ህይወት እንደነበረው እናያለን።

ፍሬድሪክ አንቶኒ ራቪ ኩማር ዘካሪያስ 1946 ዓ.ም በመድራስ ግዛት ውስጥ የሐዋርያው ቶማስ የህይወቱ መጨረሻ በነበረችው ከተማ ተወለደ። እናቱ ኤዛቤላ አስተማሪ ስትሆን አባቱ ኦስካር እንግሊዝ ኖንሃም ዩኒቨርስቲ የሌበር ሪሌሽን ትምህርት ርፍ ላይጥናት ያደረገ ነበር።

በአስተዳደጉ ዘካሪያስ ከመጻሐፍት ይልቅ የኪርኬት አፍቃሪ የነበር ቢሆንም ልዩ ችሎታን ከዘር የወረሰው እስኪመስል ድረስ ልዩ ተስዕጦ ለትምህርቱ ነበረው። ይህም ብቻ ሳይሆን ለሐይማኖቱም ትልቅ ቆራጥነት እና መሰጠትን

ከቤተሰዎቹ ተካፍሏል። ከርላ በምትባል የህንድ ግዛት ቅድመ አያቱ እና አያቱ የ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያውን ከማላይማ ( ህንድ ውስጥ ከሚነገሩ ቋንቋዎች አንዱ) ወደ እንግሊዘኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት ትርጉም አዘጋጅተዋል ይህም የመጀመሪያው የማላይማ ቋንቋ የመጻሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሲሰራ ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረው። ወደ ኋላም ስንመለከት የዘካሪያስ ቅማንት በሂንዱ ሃይማኖት የመጀመሪያ ደረጃ የነበረውን የናቡድሪን መደብ ወደ ክርስትና በመምጣት አስደነገጠች በዚህም ለዘካሪያስም ሆነ ለቤተሰቡ አዲስን የጉዞ መስመር ወደ ክርስትና ዘርጋች። ዘካሪያስ የእግዚአብሔር እጅ በቤተሰቡ እና በዘሩ ላይ ሲሰራ በብዙ ተመልክቷል። ይህም ወደ መሰረተው ተቋም ራቪ ኢንተርናሽናል ሚኒስትሪስ እንዲሁም ትውልድ እና ባህል ተሻጋሪ የሆነ የወንጌል ልብ እንዲኖር አድርጓል።

ራቪ ኢንተርናሽናል ሚኒስትሪስ ከተጀመረ 36 ዓ.ም ያስቆጠረ ሲሆን በዘካሪያስ ቤት ውስጥ ተጀምሮ የነበረው ይህ አገልግሎት በወቅቱ አንድ ተናጋሪ ወይም አስተማሪ ብቻ የነበረው ሲሆን ዛሬ በ15 ሃገራት 5 አህጉራት ከ100 በላይ የሚሆኑ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ወንጌልን የሚሰብኩ ተናጋሪዎች አሉት።

ዘካሪያስ ወንጌልን ወደ ህዝቦች ሁሉ ይዞ የመሄድ ጥማት አንገብጋቢነት የተጀመረው በቬትናም እንደ ኤ.አ በ1971 ዓ.ም ነበር ። ዘካሪያስ በ1966 ዓ.ም ካናዳ ገባ በዛም በሃይድራባድ የወጣት ለክርስቶስ አገልግሎት የስበከት ውድድር ማሸነፈ ቻለ። በዚህም ወቅት ሩት ጄፍሪ የተባለች ቬትናም ውስጥ የእንስሳ ሐኪም የነበረች ሚሲዬናውት ስብከቱን በሰምታ ግብዣ አቀረበችለች፡

ራቪ ዘካሪያስ በ 25 አመቱ ቬትናም በጦር አውሮፕላን ታጅቦ በጦር ካምፕ ፣ በሆስፒታል እና በማረሚያ ቤቶች ውስጥ ወንጌልን መስበክ ጀመረ። በዚህም ወቅት አብዛኛውን ግዜ ዘካሪያስ እና አስተርጓሚው ሄይን ፓም በጥይጥ ሩምታ ታጅበው ነበር ሚያድሩት። በአንድ ወቅት ወደ አንድ ገጠር ስፍራ ሲደርሱ ዘካሪያስ እና አብረውት የሚጓዙ ሰዎች የነበሩበት መኪና ተበላሸ። ከሰዓታት በሆላ በዚያ ስፍራ ብቅ ያለው አንድ መኪና የተባበሩን ጥሪያቸውን ችላ ብሎ አለፋቸው ። በመጨረሻም የመኪናውን ሞተር አስተካክለው ጉዞ ቀጠሉ ከተወሰኑ ኪ.ሜ በሆላ ያእነርሱን አልፎ የመጣ መኪና በጥይት ተበሳስቶ እንዳልነበር ሆኖ አገኙት በውስጥ የነበሩም አራት ሰዎች ሞተው አገኞቸው ። ይህን ግዜ ሲያስታውስ ዘካሪያስ "እግዚአብሔር ጊዜያችን ካልሆነ መንገዳችንን ያስቆማል እናም ሲሆን ደግሞ ይመራናል " ብሎ ይናገራል። ከቀናት በኃላ ዘካሪያስ እና አስተርጓሚዎቹ ቬትኮንጎች የጦር ቀጠናውን አልፈው በገቡ ጊዜ የተገደሉ ስድት ሚሲዬናውያን አገኙ ። ዘካሪያስ የተወሰኑትን ሚሲዬናውያን ያውቃቸው ነበር ።።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል ....

የቀጠለ ....

<u>እስልምና ሲፈተሽ</u>

ከክርስትና ጋር ሲነጻጸር አንዳንድ ተመሳሳይነቶች ይኖራሉ ነገርግን ብዙ መሰረታዊ የሚባሉ ልዩነቶች ግን አሉ። እንደ ክርስትና ሁሉ አስልምና በአንድ አምላክ ላይ ያምናሉ (ሞኖቴስቲክ ) ነገርግን መስሊሞች አንድ አምላክ በሶስት አካላት ተገለጠ የሚለውን የሥላሴ አስተምህሮ አይቀበሉም:: ሙስሊሞች ዋና ከሚባሉት ነቢያት ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ አንዱ እንደሆነ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አያምኑም። ሙስሊሞች ክርስቶስ ከድንግል እንደተወለደ፣ ልክ እንደ አዳም እንደተፈጠረ ይናገራሉ፣ ሙስሊሞች ክርስቶስ በመስቀል እንደተሰቀለ አያምኑም፣ አላህ (አምላክ) ነቢዩን ኢሳ( በቁርአኑ ውስጥ ለክርስቶስ የተሰጠ ስም) እንዲህ አይነነት አሰቃቂ ሞት እንዲሞት እንደሚፈቅድ አይገናቸውም ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ (በኢሳያስ 53:5-6፣ ዩሐንስ 3: 16፣ 14:6-1፣ ጴጥሮስ 2:24) እነደሚያሳየው አንዴት ፍጹም የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጆችን ሐጢያት ለመክፈል ወሳኝ እንደነበር ያሳየናል ።

እስልምና እንደሚያስተምረው ቁርአን የመጨረሻው ስልጣን ያለው እና የአላህ የመጨረሻ መገለጥ እንደሆነ ነው። በእነዚህ መሰረታዊ እና ወሳኝ የሆኑ ልዩነቶች መሰረት እስልምና እና ክርስትና ሁቱም እውነት ሊሆኑ አይችሉም። መጸሐፍ ቅዱስ እና ቁርአኑም ሁለቱም የእግዚአብሔር ቃል ሊሆኑ አይችሉም ። እውነቱ ዘላለማው ውጤት ይኖረዋል።

በአለማችን 1.7 ቢሊዬን ሙስሊሞች እንዳሉ ጥናቶች ያሳያሉ ብዙ ሰው ጠጋ ብሉ ከተመለከተው በአለም ዙሪያ ያሉ ሙስሊሞች ከሚያራምዱት አስተምሮ አንድነት በዘለለ የሚያራምዱት ስርአት አንድ አይነት ሊባል የሚችል ነው ። ይህ ደግሞ በምዕራብ አለም፣ ሩቅ ምስራቅ፣ አፍሪካም በሌሎቹም የተቀረው አለም የምናገኛቸው ሙስሊሞች ከአስተምህሮ የዘለለ የተገነባ በህል አላቸው ስለዚህም ነው ብዙ የወንጌል አስተማሪዎች ሙስሊሞችን ለማድረስ ባህሉን ማወቅ በጣም ወሳኝ ነው ብለው የሚናገሩት። ከዚህም ሀሳብ ተነስተው ብዙዎች እስልምና 10% አስተምህሮ 90% ባህል ነው ብለው የሚያወሩት:: ስለሆነም ሙስሊምን ከስነመለኮት እና አስተረምህሮአቸው አንጻር ብቻ መመልከት በቂ ስለማይሆን ከባህል አንጻር ማየት አስፈላጊ ነው።

ሙስሊሞች ቁርአኑን በጥልቅ የማያውቁ ናቸው ምን ማለት ነው? ከልጅነታቸው ጀምር ቁርአን መቅራት (መሸምደድ እና በቃል መናገር) ትልቅ የቤት ስራቸው ናቸው። ይህ ማለት ግን የሚያወሩትን በውስጣቸው አሰላስለው፣ ተረድተውት እና አምነውባቸው የሚሏቸው አይደሉም። ስለሆነም ቁርኣኑ ውስጥ ያሉትን ብዙ ስህተቶችን ባለማወቅም የሚኖሩ ናቸው።አብዛኛው የወንጌል አማኝ ብቻ ሳይሆን ብዙ ሰው እስልምናን እንደ ሐይማኖት ብቻ መረዳት ይቀናቸዋል። እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው እስልምና ሐይማኖት ብቻ ሳይሆን ባህልም ጭምር እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል ይህ ምን ማለት ነው።

ሙስሊሞች የሚተገብሯቸው እና የሚናገሯቸው ሁሉ ከቀርኣኑ የሚወጡ አይደሉም ብዙ ሰው ሐዲዝ ስለሚባሉት ሐይማኖታዊ እና የነቢዬ ሙሐመድ የህይወት ታሪክ ላይ ተመርኩዘው ስለተጻፉት መጸሐፎች እውቀት የለውም። የእስልምና አስተምህሮዎች እና ልምምዶች የአላህ(አምላክ) መገለጥ ነው ከተባለው ከቁርኣኑ የወጣ ሳይሆነ ከሐዲዞችም ጭምር ነው። እነዚህ መጸሐፎች ደግሞ በብዙ ዘመናት ሒደት የተጻፉ እጅግ ብዙ ሺ መጸሐፍች ብቻ ሳይሆኑ ፣ አብዛኞቹ ከቁርኣኑ ጋር የሚጣረሱ እውነቶችን የያዙ፣ ስለ ነቢዩ ሙሐመድ ታሪክ እና ህይወት የተደባለቁ እውነቶችን ያሰፈሩ ናቸው።

በዚህም የተነሳ በተለያዩ ግዜ ከአለም በእስልምናው አለም ሊህቃን የተባሉ ሰዎች ተሰብስበው እነዚህን መጽሐፍት ለማጥራት እና አንዳንዶቹንም ለማስወገድ ተሞክሯል ሆኖ ግን ዛሬም ድረስ በሰው እጅ ያሉ ከ60,000 በላይ ሀዲዞች እንዳሉ ይነገራል።

ብዙ ሰዎች እስልምና አንድ አሰተምሮ ያለው አንድ ሐይማኖት ብቻ ይመስላቸውል:: ነገር ግን እሰልምና በውስጡ በአስተምሮ እና በልምምድ የተከፋፈሉ ቡድኖች አሉት። የእነዚህ ቡድኖች መከፈል በመጀመሪያ የፖለቲካ ሁኔታዎች የፈጠሩት ቢሆንም ከዚያ በሁዋላ የአስተምህሮ እና የልምምድ ልዩነቶች ተጨምረው ሰፍተዋል። በዚህም መሰረት ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ሲኖሩት ሱኒ ፣ ሺሃ እና ካራጃይትስ ይባላሉ:: ከእነዚህም ሺሃ ሙስሊሞች ውስጣቸው በሌላ ቡድኖች የሚከፈሉ ናቸው እነርሱም አስራሁለቶቹ ( በአስራ ሁለት ኢማሞች የሚያምኑ እና ነቢዩ ሙሐመድ ይኖረኛል ካሉት እስራ ሁለት ተረካዎች በሐዲዞችም ላይ ከሚገኘው አስተምህሮ በመነሳት የያምኑ ናቸው)፣ ኢስማይሊዝም በውስጡም ( ናዛሪ፣ ሰቪነር፣ ሙስጣሊ፣ ዳዎዲ ቦሃር፣ ሃብቲሃስ ቦሃር፣ ሱላማኒ ቦሃር እና አላቪ ቦሃር ናቸው) ፣ ዛዲያህ ( በታሪክ ዛይድ ኢበን አሊን ይከተሉ ከነበሩ ሰዎች የመጣ ነው )፣ አላዊተስ (አነዚህ በዘጠነኛው እና አስረኛው ክፍለዘመን የተጀመረ ነው)፣ ድሩዝ ( በአስራአንደኛ ክፍለ ዘመን የተጀመሩ ሲሆን ከእስልምና አፈንግጠው እንደወጡ የሚታሰቡ ናቸው በዚህም እንደ ሙስሊም የሚቆጠሩ አይደሉም)።

እንደ ወንጌል አገልጋይ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመጨመር የመጀመሪያው አስፈላጊው ላልዳኑ ሰዎች የሚኖረን ልብ እና ፍቅር ነው። ላልወደድነው እና በህይወታችን ቦታ ላልሰጠነው ነገር ዋጋ ልንከፍል አይቻለንምና። ሰዎችን የማዳን ስራ ደግሞ በድንገት የምንሰራው ስራ ሳይሆን "በሆንብሎኝነት" የምንሰራው የቤት ስራ መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ ይህ ምንድነው ግዜያችንን፣ አቅማችንን፣ እውቀታችንን፣ ጉልበታችንን እና ልባችንን ልንሰጠው ያስፈልጋል ማለት ነው። ትልቅ የወንጌል ትኩረት ሊሆን ከሚገባ አንዱ ጉዳይ ደግሞ የሙስሊሞች በወንጌል መደረስ ነው:: ይህን ለማድረግ ማንኛውም አማኝ “ሙስሊሞች ማን ናቸው ? እምነታቸው ምንድን ነው? እስለምናን ከክርስትና ምንድነው ሚለየው? ስለ ሙስሊሞች ምን ልወቅ?” የሚሉትን መረዳት ይህን ህዝብ በወንጌል ለመድረስ ትልቅ አቅም ነው ብዬ አምናለሁ ። ክርስቶስ ኢየሱስ በውርንጭላ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በሚገባበት ወቅት መጸሐፍ ቅዱስ አንድ ነገር ይላል እንደ ጠፉ በጎች ተቅበዝብዘው ባያቸው ግዜ አዘነላቸው አለቀሳለቸውም ይላል ይህን ልብ ሳንይዝ ጎረቤቶቻችን፣ ቤተሰቦቻችን እና ጓደኞቻችን ለሆኑ ለሙስሊሞች ክርስቶስን መስጠት አንችልም።

የእስልምናን ስሁትነት የሚያጋግጡ የእስተምሮ እና ልምምድ እውነቶችን ማወቃችን እነዚህን ሰዎች በወንጌል ለመድረስ ትልቁ ጉዳይ አይደለም። አንድን ወንድ እና ሴት በእስልምና ውስጥ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። የብዙ አማኞች ችግር ሙስሊሞችን ለመረዳት ሆነ ስለ እስልምና ለማወቅ ፍቃደኛ አለመሆናችን እና ለማወቅ ጥረት አለማድረጋችን ነው። ማወቃችን እነዚህን ህዝቦች በወንጌል ለመድረስ ቢረዳን እንጂ ምንጎዳው አለ ብዬ አላስብም።

በመጨረሻም ጌታችን እና መድሃኒታች ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድ የሚወድ መውደዱንም በመስቀል ላይ በመሞት የገለጠ አምላክ ነው። ወደ አለም ሁሉ ሂዱ የሚለውን ትዕዛዝም የተቀበልነው ከእርሱ ነውና ወንጌል የማድረስ የቤት ስራችንን እንድንወጣ አሳስባለው።

አማኑኤል ገዛኸኝ (የተልዕኮ አስተማባሪ )

አርትኣት፡ ፡ ናኦል በፍቃዱ

# እስልምና እና ክርስትያናዊ ተልዕኮ (ሙስሊሞችን በወንጌል የመድረሻ ስልቶች)

ለክርስትና እና ክርስቲያናዊ ተልዕኮ እንደ እስልምና ያለ ትልቅ ፈተና የለም። በዚህ ድምዳሜ አብዛኞቹ የሚስዮን አጥኚዎች ይስማማሉ። እስልምና ከተነሳበት ከ 7ተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ለክርስትና ትልቅ ፈተና ሆኖ ሰንብቷል። ከ 1.6 ቢልዮን በላይ ተከታዮችን በማፍራት ከክርስትና ቀጥሎ ብዙ ተከታዮች ያሉት እምነት ነው።

በአለማችንም ቢሆን በአገራችን የእስልምና እና የሙስሊሞች ተፅዕኖ ከ ጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል። ለአብነት በአሜሪካ በተለይ ከ በመስከረም 11 ፤ 2001 እአአ በአሸባሪዎች ከደረሰው የመንትዬዎቹ ሕንፃዎች ውድመት በኋላ እስልምናን ለመረዳት ከፍተኛ ጉጉት በሰዎች ላይ እንዳደረ ይገለፃል። አንድ ጥናት እንደሚያሳየው በአሜሪካ በቀን ከ10,000 (አስር ሺህ) በላይ ሰዎች ከሌላ ሐይማኖት ወደ እስልምና ይቀየራሉ። የእስልምና ተፅዕኖ ከዚህም አልፎ በአሜሪካ ኮንግረስ መከራከሪያ ሃሳብ እንዲሁም ፖከቲካው ላይ ተፅዕኖ ያሳደረ ጉዳይ ሆኗል።

በሀገራችንም እንዲሁ ነው። እስልምና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ ሰባተኛው ክፍለዘመን እንደሆነ ይነገራል። የ ነብዮ ሙሐመድ ልጅ ሩቅያ ከተከታዮቻቸው ጋር በስደት ወደ ኢትዮጵያ ስትመጣ የተቀበላት የአክሱም ንጉስ ነጋሲ (ኋላም ወደ እስልምና ተቀይሮ ነጋሽ ተብሏል) ነበር ይበላል። ከዚያ በኋላ እስልምና በተለያዪ በሀገራችን ውስጥ በነበሩ ሕዝቦች እንደ አዳል ፣ ኢፋት ወዘተ ያሉ በደቡበ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍል በሚኖሩ አንዳንድ ሕዝቦች ተከታዮች እንደነበሩ ታሪክ ይናገራል። የእስልምና ግዛቶች ከሰሜኑ የክርስትያን አቢስኒያ ስርወ መንግስታት ጋር በታሪክ ጥሩ ግንኙነት አልነበራቸውም። እስልምና በአህመድ ጉረይ (ግራኝ አህመድ) አማካይነት የሐረር እና አዳል ሱልጣኖችን በማስተባበር እንዲሁም የአፋር ፣ ሐረሪ እና ሶማሌ ሕዝቦችን በማስተባበር በ16ኛው ክፍለ ዘመን የሰሜኑን የክርስቲያን ግዛት ለመውረር ጥረት ቢያደርግም ከብዙ ጦርነቶች በኋላ ሳይሳካለት ቀርቷል። በተመሳሳይ የሰሜን ክርስቲያናዊ ስርወመንገስታት ነገስታትም የእስልምና ግዛቶችን ለመውረር ጥረት አድርገው ሳይሳካላቸው ቀርቶ በመጨረሻም በንጉስ ምኒሊክ ፪ በ 19ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ ተሳክቶላቸዋል። የኢትዮጵያ ሙስሊም ፀሃፍት እስልምና በኢትዮጵያ ነገስታት እና መሪዎች (ከአፄ ዮሃንስ ፬ ጀምሮ እስከ አህአዴግ ድረስ) ሲጨቆን እንደኖረ ይናገራሉ። በእርግጥም ታሪክን በሃቅ ለመዘነ ሙስሊሞች በኢትዮጵያ በሐይማኖታቸው ምክንያት ሲጨቆኑ እንደነበር ለማረጋገጥ አይከብድም።

በአሁኗ ኢትዮጵያ ሙስሊሞች በሀገሪቱን አንድ ሶስተኛ ሕዝብ ይሸፍናሉ። በቅርብ ጊዜያት ደግሞ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ከሆኑት መካከል ከፖለቲከኞች እና ባለስልጣናት እንደ ጃዋር መሐመድ (ፖለቲከኛ) ፣ ደመቀ መኮንን (ም/ጠ/ሚ) ወዘተ ያሉት የእስልምና እምነት ተከታዮች ናቸው። ይህ ብቻም አይደለም ከዘጠኙ የክልል ፕሬዝዳንቶች መካከል አራቱ ሙስሊሞች ናቸው። በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስትሩም የተገኙት ከእስልምና ቤተሰብ መሆኑ ይታወቃል። እስልምና ከሌላው ጊዜ በተሻለ እውቅና ያገኘበት ጊዜ ነው።

በኢትዮጵያ እስልምናን እና ሙስሊሞች ላይ ትኩረት ያደረገ ክርስቲያናዊ ተልዕኮ የጀመረው በ20ኛው ክፍለ ዘመን ነው። በእርግጥ በ19ኛው ክፍለዘመን ማገባደጃ ላይ በእነ ወንድም ንጉሴ ጅማ ላይ ጥቂት የወንጌል እንቅስቃሴ ጅማሮ ነበር። አባ ጅፋር ግራ ዘመም የሆነ አስተሳሰብ ስለነበራቸው ወደ ጅማ የመጡትን ሚስዮናውያም እንደተቀበሏቸው አንዳንድ የታሪክ ዘገባዎች ያሳያሉ። በጅማ የነበረው እንቅስቃሴ ግን ገፍቶ አልቀጠለም።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን አፄ ሃይለስላሴ የውጭ ሚስዮናውያን ኦርቶዶክስ ያልደረሰችበትን የሀገሪቱን ክፍል ይድረሱ የሚል ትዕዛዝ በ1939 እአአ በማውጣታቸው ምክንያት በጊዜው በኢትዮጵያ ይንቀሰቀሱ የነበሩ ሚስዮናውያን እንደ Sudan
Interior Mission (SIM) ፣ Swedish Evangelical Mission (SEM).፣ American Presbyterian Mission ወዘተ ያሉት ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል እንዲሰሩ ፈቃድ ተሰጣቸው። ከእነዚህ መካከል ታዲያ እስልምና ላይ ትኩረት ያደረገው የ Sudan
Interior Mission (SIM) ድርጅት ነበር። SIM በደቡብ ወደ አሩሲ እና ባሌ ኦሮሞ ሙስሊሞች እንዲሁም በምስራቅ ወደ ኦጋዴን ሶማሌ ሙስሊሞች ዘንድ ተልዕኮ እንደነበረው ታሪክ ይናገራል።

ስለ እስልምና ፣ አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተፅዕኖ እንዲሁም እስልምናን መሰረት ስላደረጉ ታሪካዊ ተልዕኮዎች ይህንን ካልን አሁን ደግሞ እስልምናን ለመድረስ ሚስዮናውያን እንዲሁም ክርስትያኖች በአጠቃላይ የሚጠቀሟቸውን ስልቶች በአለም አቀፍ እንዲሁም በምስራቅ አፍሪካ አውድ እንምልከት።

## <u>እስልምናን በወንጌል የመድረሻ ስልቶች</u>

በታሪክ እስልምና አለም ከተሰማሩ ክርስቲያን ሚስዮናውያን መካከል የ 13ኛ ክፍለ ዘመኑን ስፔናዊውን ካቶሊክ ሚስዮናዊ ሬይመንድ ሉል የሚያክል እንደሌለ ብዙ ፀሃፍቶች ይስማማሉ። ሬይመንድ ሉል በ 13ኛው ክፍለ ዘመን ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ ወደ አረብ ያቀና ሲሆን በጊዜው ብዙ ፍሬ እንዳየ ተዘግቧል። ከ ሉል ቀጥሎ ሌላኛው ተጠቃሽ ሰው የ19ኛ ክፍለዘመን መባቻ እና 20ኛ ክፍለዘመን ላይ ያገለገለው ሳሙኤል ዝዌመር ነው። ሳሙኤል ዝዌመርም እንዲሁ ብዙ ፍሬ እንዳየ ይታወቃል። በሃያኛው ክፍለዘመን ብዙ የሚስዮን ጉዞዎች ወደ መካከለኛው ምስራቅ እና ወደ እስያ ተደርገዋል። አብዛኞቹ የእስልምናውን አለም ለመድረስ ያለሙ ነበሩ።

ወደ እስልምና አለም የሚሰማሩ ሚስዮናውያን እና አገልጋዮች ሁሉም ታዲያ አንድ አይነት ስልትን አይጠቀሙም። አብዛኞቹ የተላኩለት ሕዝብን ለመድረስ ይበጃል ያሉትን ስልት ይጠቀማሉ።

እስልምናን ለመድረስ በአብዛኞቹ ሚስዮናውያን እና ክርስትያኖች የሚመረጡትን ስልቶች በአጠቃላይ በሁለት መክፈል እንችላለን። እነሱም ትችታዊ ፣ አውዳዊ ፣ መለኮታዊ መገለጥ እና መለኮታዊ ተዐምር ብለን ልናያቸው እንችላለን። አንድ በአንድ እንመልከታቸው።

## 1) ትችታዊ ስልት (Polemics)

ይህ ስልት በቤተክርስትያን ታሪክ በብዛት ሲዘወት የቆየ ስልት ሲሆን የእስልምናን ደካማ ጎን በማግኘት እስልምናን በመተቸት ሙስሊሞችን ከእስልምና መለየት ሲሆን ሃሳቡ። በክርስትና ላይ ቆመን እስልናን ከተቸን ሙስሊሞች ወደ ክርስትና መምጣታቸው አይቀርም የሚል መነሻ ሃሳብ አለው። ስለዚህም ትችታዊ ስልት ከክርክር ሙስሊሞች ወደ ክርስቶስ
የትችታዊ አካሄድ ደጋፊዎች የሐዋርያው ጳውሎስን እና የ ክርስቶስን ክርክሮች ከመፀሐፍ ቅዱስ እንደማስረጃ ይጠቅሳሉ። ስለዚህም ሙስሊሞችን ለመድረስ የግድ ቁርዓን ስሁት ሙሐመድ ደግሞ ውሸተኛ ነብይ እንደሆነ ማሳየት አለብን ብለው ያምናሉ።
ከዚህ አስተሳሰብ ደጋፊዎች መካከል በታንዛኒያ ለአምስት አመት ሚስዮናዊ የነበረው እንግሊዛዊው ጀፀይ ስሚዝ ይታወቃል። ከእርሱ በተጨማሪ ዴቪድ ውድ ፣ ሳም ሻሙን ፣ ሮበርት ስፔንሰር ፣ ክርስቲያን ፕሪንስ ወዘተ የተባሉ የስነመለኮት ሰዎች ይጠቀሳሉ። ከዚህኝ በተጨማሪ አብዛኛው የምዕራብ የስነመለኮት ሰዎች ይህንን መንገድ ይመርጣሉ።
በሀገራችንም በዚህ ላይ የተሰማሩ ፀሃፍት አሉ። እንደ አንዋር ሰይድ ፣ ዶ/ር እውነቱ ፣ ዲሰን መንዲድ (የብዕር ስም) ፣ ሳሂህ ኢብራሂም (የብዕር ስም) ይገኙበታል።
እዚህ ላይ የሚነሳው ትችት ግን ይህ መንገድ ምንም እንኳ ለምዕራባውያን ካላቸው ነፃነት አንፃር ምቹ ቢሆንም በአፍሪካ እና በእስያ ላሉ ክርስቲያኖች እና ሚስዮናውያን ግን እስልምናን በአደባባይ መተቸት ወይም መቃወም ብዙ ዋጋ ሊያስከፍል እንደሚችል ነው። የክርክር እና የውይይት ልምዱ በሶስተኛው ዓለም ደካማ ከመሆኑም በላይ ብዙ ፅንፈኛ የእስልምና እምነት ተከታዮች እና አሸባሪዎች በእነዚህ አከባቢ ሊኖሩ ስለሚችሉ ሚስዮናውያኑ እና ክርስቲያኖች ላይ ጥቃት ይደርሳል። በሀገራችንም እስልምናን በመተቸት የሚፅፉ ሰዎች የብዕር ሰም የሚጠቀሙት ከዚሁ መነሻ ነው።
ስለዚህም ይህንን መንገድ ሁሉም ቦታ መተግበር ይከብዳል ብለው ተቺዎች ምክንያታቸውን ያስቀምጣሉ።

## 2) አውዳዊ ስልት (contextualization)

የዚህ ስልት ተከታዮች ደግሞ መነሻቸውን በእስልምና ስህተት ላይ ሳይሆን በክርስትና እና በእስልምና መመሳሰል ላይ ያደርጋሉ። ይህንን የጋራ መሰረት ተጠቅመው ወንጌሉን ለሙስሊሞች ለማድረስ ይጥራሉ።
ይህ ስልት የክርስቶስ ተሰግዎ (ስጋ መልበስ) እንደ ምሳሌ ያያል ክርስቶስ ስጋ ሲለብስ እኛን እየመሰለ እና ከሰው ልጆች ጋር ለመግባባት የጋራ መሰረት እንደጣለ ሁሉ እኛም ሙስሊሞችን ለመድረስ የጋራ መሰረት መጣል አለብን ብለው ያምናሉ።
ከእስልምና ጋር የጋራ መሰረት አለን ወይ? ለሚለው ጥያቄ መልሰ «አዎን አለን ያውም ብዙ» ብለው ይመልሳሉ የስክቱ ተከታዮች። ከጋራ መሰረቶች መካከልም የመጽሐፍ ቅዱስ እና የቁርዓን ታሪኮች መመሳሰል፣ ተመሳሳይ ግለሰቦች መኖራቸው ፣ ቁርዓን ስለኢየሱስ የሚናገራቸውን መልካም ነገሮች እንደ አብነት ያነሳሉ። እነዚህን እንደመነሻ በመጠቀም ለሙስሊሞች ወንጌልን ማድረስ እንደሚቻል ይናገራሉ።

የዚህ አስተሳሰብ ተከታዮች በምዕራቡ አለም የ ሚስዮን አስተማሪዎች ሲሆኑ አብዛኞቹ በእስልምና አለም የተሰማሩ ሚስዮናውያን ይህንን አካሄድ ይቀበሉታል ብሎም ፍሬያማ እንደሆነ እና ከሚስሎሞች ጋር ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት እንደማይረብሽ እንደውም እንደሚያስቀጥል ይመሰክራሉ።
በሀገራችንም እንደ 10/40 አለም አቀፍ ተልዕኮ (ኢትዮጵያ ገነት ቤ/ክ) ፣ ሆርን ኦፍ አፍሪካ ሚሽን ኢንጌጀርስ ፣ አርክ ሚኒስትሪስ ወዘተ ያሉ የሚስዮን ድርጅቶች ይህንን አካሄድ ይመርጡታል።
የዚህ ስልት ደካማ ጎኑ ሚስዮናውያንን የክርስትና ጣዕም የሆነውን ስደትን እንዳይቀምሱ በማድረግ ፈሪ ያደርጋቸዋል የሚል ነው። ይህ ስልት ከሌሎቹ አንፃር ከሙስሊሞች ዘንድ ብዙም ተቃውሞ ስለማያስነሳ ይህንን የሚመርጡ ሚስዮናውያን ፈሪዎች እና ለክርስቶስ ያልቆረጡ ናችው ተብለው በአንዳንዶች ይተቻሉ።
ከዚህም በተጨማሪ ይህ አካሄድ ከተለጠጠ ክርስትናን ከእስልምና ጋር በመቀየጥ ሌላ ሃይማኖት ሊሰጥ ይችላል የሚል ፍራቻ ያላቸውም አሉ። ለዚህም አውዳዊነቱ እስከምን ድረስ ነው? የሚለው አከራካሪነቱን እንደ ማስረጃ ይጠቅሳሉ።

## 3) መለኮታዊ መገለጥ (Divine Revelation)

ይህንን አስተሳሰብ የሚከተሉ ደግሞ ሙስሊሞችን በአውዳዊም ሆነ በክርክር ወደ ክርስቶስ ማምጣት አይቻልም። ብቸኛው አማራጭ እግዚአብሔር ራሱን እንዲገልጥላቸው መፀለይ ነው የሚል ነው።
የዚህ አስተሳሰብ ተከታዮች ሙስሊሞች በንግግር ወደ ክርስቶስ እንደማይመጡ እና ጌታ ኢየሱስ ለአሰ ዳጄ ለሳውል በደማስቆ መንገድ እንደተገለጠ እንዲሁ ለሙስሊሞችም ካልተገለጠ በቀር ወደ ክርስቶስ እንደማይመጡ ያምናሉ።
እነዚህ ሰዎች የብዙ አረብ ሙስሊሞች ምስክርነትን እንደምሳሌ ያነሳሉ። ብዙ የአረብ ሙስሊሞች ወደ ክርስቶስ የመጡበትን ታሪክ ሲገልፁ «በህልም ተገልጦልኝ» ፣ «ኢየሱስን በራዕይ አይቼው» ወዘተ የሚሉ ነገሮችን ሲናገሩ ይደመጣል። አብዛኞቹ ሙስሊሞችም እንደዚህ አይነት ራዕይ እንደሚያዩ የተለያዩ ምሰክርነቶች ያስረዳሉ።
የዚህ አስተሳሰብ ተከታዮች በተለያዩ የአለማችን ክፍል የሚገኙ ሲሆን በፀሎት ሃይል የሚያምኑና ከፀሎት ጋር ለሙስሊሞች ፍቀርን በማሳየት ብቻ የሚወዳጁ ናቸው። በሚያሳዩት ፍቅር እና በሚፀልዩት ፀሎት ክርስቶስ ራሱን ለ ሙስሊሞች እንደሚገልጥ ያምናሉ።
የዚህ አስተሳሰብ ችግሩ ደግሞ ሙስሊሞች በወንጌል ምስክርነት ሊድኑ አይችሉም የሚለው ድምዳሜው ነው። ምንም እንኳ አብዛኞቹ ሙስሊሞች ራዕይ ወይንም ህልም አይተው ወደ ክርስትና ቢመጡም አስቀድሞ ግን በወንጌል ምስክርነት የተዘራባቸው የወንጌል ዘር እንደሚኖር ልንዘነጋ አይገባም። ከዚህም ባለፈ እንደ ጳውሎስ የደማስቀ መንገድ ላይ ክስተት ወደ ክርስቶስ የሚመጡ እንዳሉ ሁሉ በ ሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ወደ ክርስቶስ የመጡ ብዙዎች እንዳሉ መዘንጋት የለብንም። ሚስዮናውያን በስራቸው ፍቅር እንዲያሳዩ ብቻ ሳይሆን በአንደበታቸውም ወንጌሉን እንዲመሰክሩ ያስፈልጋል። በመጋቢ ጆን ፓይፐር አገላለፅ «የዳንነው በስራ ስላልሆነ ሰዎችም የእኛን ስራ አይተው ሊድኑ አይችሉም። እምነት ከመስማት ነውና የግድ ወንጌሉ ሊነገራቸው ያስፈልጋቸዋል።»

**4) የመለኮት ጣልቃ ገብነት (Divine Intervention)**

እነዚህ ከ«መለኮት መገለጥ» ስልት ተከታዮች የሚለዩት ራዕይ ወይንም ህልም ለሙስሊሞች እስኪገከጥ አይጠብቁም ይልቅስ ሙስሊሞችን ጋር ያሉ ችግሮችን (በሽታ ፣ ረሃብ ፣ ወዘተ) በ መለኮታዊ ሃይል በመፈወስ ወይንም በመድረስ ሙስሊሞችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት የሚለውን ይከተላሉ። ስለዚህም ስብከት እና ክርክርን ወይንም አውዳዊነትን ከመከተል ይልቅ ተዐምራትን በማድረግ ብዙ ሙስሊሞችን በቀላሉ ወደ ጌታ ማምጣጥ ይቻላል ብለው ያምናሉ።

ለሀሳባቸው መደገፊያ የ ጌታ ኢየሱስን እንዲሁም የሐዋርያቱን የተዐምራት ህይወት እና እንዴት ብዙዎች በአንድ ጊዜ ብዙዎች በተዐምራት ወደ ክርስትና እንደመጡ በማስረጃነት ያሳያሉ። መንፈሳዊ ስጦታዎች የተሰጡት ለአካሉ (ለቤ/ክ) እስከሆነ ድረስ ሁሉም እነዚህን ስጦታዎች ሊጠቀም ይችላል። በተለይ ደግሞ ሚስዮናውያን ለወንጌሉ መድረስ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

የዚህ አስተሳሰብ ተከታዮች በተለይ በአፍሪካ እጅግ ብዙ ናቸው። ይህም ከ 20ኛው ክፍለ ዘመን የጴንጤቆስጤያዊ እንቅስቀሴ ጋር ይገናኛል። የዚህ አስተሳሰብ ደጋፊ ከነበሩት መካካል እጅግ ታዋቂው በዚህ አመት ወደ ጌታ የሄደው ጀርመናዊ ወንጌላዊ ሬይንሃርድ ቦንኬ ይገኙበታል። ቦንኬ በተለይ በናይጄርያ በእርሳቸው የተዐምራዊ የወንጌል አገልግሎት በሚልዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ወደ ክርስቶስ እንደመጡ ተናገረዋል። በአፍሪካ ይህ አስተሳሰብ እንዲሰፋ የወንጌላዊ ሬይንሃርድ ቦንኬ ሚና ቀላል አይደለም።

በሃገራችንም እጅግ ብዙ ወንጌላውያን ፣ ነብያት እና ሐዋርያት የዚህ አስተሳሰብ ተከታዮች ናቸው። ለምሳሌ በዚህ አግልግሎታቸው የሚታወቁ እንደ ወንጌላዊ ሰለሞን ከተማ ፣ ሐዋርያው ንጉሴ ሮባ (በተለይ በአርሲ ሙስሊሞች ዘንድ በዚህ አገልግሎት የሚያገለግሉ) ፣ ሐዋርያው አክሊሉ ወዘተ ይገኙበታል። በፍሬያቸውም ብዙ ሙስሊሞች ወደ ክርስትና እንደመጡ ይናገራሉ።

የዚህ አስተሳሰበ ደካማ ጎን ተብሎ ሊነሳ የሚችለው ቀደም ብለን ለ «መለኮት መገለጥ» ስልት ተከታዮች ካነሳነው ጋር ይመሳሰላል። ምንም እንኳ መንፈስ ቅዱስ ተዓምር አድራጊ እንደሆነና ዛሬም ድረስ ይህ ሃይሉ እንደሚሰራ እንደሆነ ግልጥ ቢሆንም ተዓምራት ግን ስብከትን ተከትሎ ይመጣል እንጂ የወንጌል ምስክርነትን ይተካል ማለት አይደለም። በሐዋርያቱም አገልገሎት የሆነውም የሚያሳየን ይህንኑ ነው። ወንጌሉን መስበክ በምንም ሊተካ አይችልም።

ይህ ብቻ ሳይሆን በዚህ መልኩ ወደ ክርስትና የመጡ ሙስሊሞች ምን ያህል ፀንተው ይቆያሉ? የሚለውም ሌላው የሚያከራክር ነጥብ ነው። በሌሎች ማህበረሰቦች ላይ በዚህ ዙርያ የተሰሩ ትናቶች እንሰሚያሳዩት ዘላቂ ክትትል እና ትምህርት ካልተደረገላቸው በቀር በዚህ መልኩ ወደ ክርስትና የመጡ ሙስሊሞችን ማቆየት እጅግ ከባድ እንደሆነ ነው። ስለዚህ የወንጌል መልዕክትን ማስቀረት የለብንም።

ሶስተኛ የዚህ ስልት ተጠቃሚዎች ሰፋፊ አዳራሾችን በመጠቀም የሚያደርጓቸው «ክሩሴዶች» በቀጠይ ጊዜያት በአከባቢው የተሰማሩ ሚስዮናውያን ላይ ጫና ሊያሳድር ይችላል። አብዛኞቹ የዚህ ስልት ተጠቃሚዎች እየተዘዋወሩ የሚያገለግሉ ወንጌላውያን ፣ ሐዋርያት እና ነብያት እንደመሆናቸው መጠን ባገለገሉበት አከባቢ በዘላቂነት አይኖሩም። በእነርሱ አገልግሎት የተበሳጩ ሙስሊሞች በአከባቢው በዘላቂነት የተሰማሩ ሚስዮናውያን ላይ በቀጣይ ጊዜያት ጥቃት ሊያደርሱ ይችላሉ። ለዚህ የመጋቢ ቤኒ ሂንን እአአ 2007 በሕንድ ባንጎግ የተካሄደውን ክሩሴድ ማየት በቂ ነው። በዚህ ክሩሴድ ላይ እስከ 7 ሚልዮን የሚደርሱ ሰዎች እንደተገኙ ይነገራል። ሆኖም በኮንፈራንሱ ማብቂያ ላይ በፕሮግራሙ የተበሳጩ የሂንዱ እምነት ተከታዮች ብዙ ውድመት አደርሰዋል። መኪናዎችን አቃጥለዋል። ከዚህም በላይ በአከባቢው ለረጅም ጊዜ ተሰማርተው የነበሩ ሚስዮናውያን ላይ በቀጣይ ቀናቶች ከፍተኛ ጫና እና መሰደድ ደርሶባቸው ነበር። ይህንን ስልት የሚጠቀሙ ሰዎች ካልተጠነቀቁ የአከባቢው ማህበረሰብ ሚስዮናውያን ላይ ሊደርስባቸው ይችላል።

የትኛው ስልት ይሻላል?

እነዚህን አራት ስልቶች ካየን አሁን የትኛው ስልት ይሻላል የሚለውን ጥያቄ እንመልስ። አራቱም ስልቶች መልካም ጎን አላቸው ደግሞም ደካማ ጎን አላቸው። አራቱም ስልቶች ብዙ ተከታዮች አሏቸው። ታዲያ የትኛው ነው የሚያዋጣው?

የዚህ ጥያቄ መልስ ሚስዮናዊው/ክርስቲያኑ በተሰማራበት የእስልምና አከባቢ ፣ ባለው የእውቀት ደረጃ እንዲሁም በግል ክህሎት እና መሰጠት ይወሰናል። በምዕራቡ አለም የሚኖሩ ሙስሊሞች ክርክርን የሚመርጡ እንደመሆናቸው ትችታዊ ስልት አዋጭ ሊሆን ይችላል። ለትችታዊ ስልት ደግሞ ስለ እስልምና ጥልቅ እውቀት ስለሚስያስፈልግ ራስን በእውቀት መገንባት ያስፈልጋል። እንዚህን እና የመሳሰሉ ነገሮችን ከግምት በማስገባት የተሻለውን መንገድ መምረጥ ይቻላል።


ከዚህም በላይ እነዚህ ስልቶች በመቀላቀል መጠቀም እንደሚቻል ልብ ሊባል ይገባዋል።

እንደማጠቃለያ በመግቢያዬ ላይ እንዳልኩት እስልምና ከጊዜ ወደ ጊዜ በአለም አቀፍም በሃገራችንም ተፅዕኖው ከፍተኛ እየሆነ ነው። ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ጎረቤቶቻችን ብቻ ሳይሆኑ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መገለጫዎችም ናቸው። ከምን ጊዜውም በላይ ቅርባችን ናቸው። መሪዎቻችን ናቸው። የእውነቱን ወንጌል ልናደርስላቸው ምን ያህል ግድ ይለን ይሆን? እግዚአብሔር ይርዳን!

**ናኦል በፍቃዱ (BTh, MA in World Mission) የወንጌል ሰባኪ ፣ የመፀሐፍ ቅዱስ አስተማሪ**

**የቀጠለ ....**





ከዚህኛው ጉዞ በኃላ ዘካሪያስ አና ባለቤቱ ማርጊ ወደ ኤሊኖይስ ግዛት ጌርፊልድ የተባለ ቦታ ላይ ተዘዋወሩ አላማውም ዲቪኒቲ ኢቫንጀሊካል ትምህርት ቤት ለመከታተል ነበር። ትምህርቱንም ሲጨርስ ኒው ዮርክ ውስጥ ያለ አሊያንስ ቲዬሎጂካል ሴሚናሪ ማስተማር ጀመር የእረፍት ቀናቱን ደግሞ እየዞረ ወንጌልን ይሰብክ ነበር። ዘካሪያስ ይህን ጊዜ ሲናገር በሴሚናሪው ይሰራው የነበረው ስራ እና የስብከት አገልግሎትቱ ሌሎችን ከጠቀመው በላይ ራሱን በብዙ የእንደጠቀመው ያወራል።

ታድያ በዚህ ግዜ ነበር በ1983 አምስተርዳም ላይ ቢሊግራሐም እንዲናገር ጥሪ ያቀረበለት ። ዘካሪያስሰ በወቅቱ ቢሊግርሃም እንኳን እርሱን ይቅርና ስብከቱን እንደሰማ አስቦትም አያውቅም ነበር። ከ133 ሃገራት የተወጣጡ

3,800 ወንጌላውያን የተሰበሰቡበት ኮርፍራንስ ላይ የትምሀርቱን መጀመሪያ ዘካሪያስ እንዲህ አለ «መልእክቴ ትንሽ ከበድ ያለ ነው›› አለ ቀጠሎም «ሐያማኖት፣ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ባህል እና ፍልስፍና በክርስቶስ መልዕክት እና በሰው ልጅ ሐሳብ መሃል ጥልቅ የሆነ መቃቃር ፈጥሯል›› ከተለመደ አይነት ለየት ያለ መልዕክት አስተጋባ ።

ይህ መልዕክት የዘካሪያስን ወደፊት የቀየረ ነበር። ይህም ብቻ ሳይሆን የእቅብተ እምነት አካሄዱንም እንደቀየረች ይታሰባል። መልዕክቱንም አቅርቦ ከጨረሰ በኃላ ረጃጅም የጥያቄ እና መልስ ቆይታዎችን ያደርግ ነበሩ። በወንጌል ማዳረስ አገልግሎት ላለመገደብም በ1980ዎቹ በአሜሪካ ብቻ ሳይሆን በአለም በተለያዩ ሃገራት የሚደርስ የራዲዬ ዝግጅት ጀመረ በዚህም ብዙዎች ለመጀመሪያ ግዜ የክርስቶስን ወንጌል ለመስማት እድል አገኙ ። ሌት ማይ ፒዩፕል ቲንክ በተሰኘ ሳምንታዊ የ30 ደቂቃ ፕሮግራም ዘካሪያስ የክርስትና መልዕክት እና መጽሐፍ ቅዱስ ተአማኒነት እና እውነትነት፣ ዘመናዊ የእውቀት ንቅናቄዎች ድካም እና የክርቶስ ልዩነት በብዙ ያስተምር ነበር ። ዛሬ ይህ የራዲዬ ፕሮግራም በ32 ሃገራት በ2000 ራዲዬ ጣቢያዎች 15.6 ሚሊዬን አድማጮችን በአመት ይደርሳል።

አገልግቱ እያደገ በመጣ ቁጥር ዘካሪያስም ፍላጎቱ ይጨምር ነበር በ1990 (እ.አ.አ) አባቱን ተከትሎ ወደ እንግሊዝ አቀና በዚያም ካሳተማቸው 28 መጸሐፎቹ መካከል የመጀመሪያው የሆነውን መፅሀፍ ለመጻፍ ቻለ። ወንጌላውያንን በአቃቤ እምነት ጠለቅ ያለ እውቀት ያልነበራቸውን ሚሲናውያንን የማሰልጠን ጥማት በተለያየ መልኩ ሲያደርገው ቆይቶ በ2004ዓ.ም (እ.አ.አ) በተደራጀ መልኩ ይሰራ ጀመር ይህም በአገልግሎቱ ወሳኝ አቅጣጫ ነበር ።

ያለፈው አመት ጥቅምት 2019 ወደ አንጎላ ካቀናበት ጉዞ በኃላ በኃላ ከራቪ ዘካሪያስ ኢንተርናሽናል ሚኒስትሪ ፕሬዘዳንትነት ራሱን አውርዶ አለም አቀፍ አግልገሎቶች እና የጽሑፍ ስራዎቹ ላይ ትኩረት ለማድረግ ወሰነ። አመራሩንም ለሴት ልጁ ሳራ እና ለረጅም አመት አብራ ላገለገለች ሚሼል ራምሰደን አስረከበ ።

PAGE 22

የወንጌሉ ሰው ፣ የእቅብተ እምነት አገልጋይ በ ግንቦት 2020ዓ.ም በተወለደ በ74 ዓመቱ፤ የ48 አመት የትዳር አጋሩ ማርጊ ሶስት ልጆቻቸው ሳራ፣ ናዮሚ ፣ ናታን ፣ አምስት የልጅ ልጆቸቸው እና ብዙ የሚወዷቸው ወዶች ከበዋቸው ወዳገለገለው እና ወደሚወደው ጌታ ሄዷል። እኔ ደግሞ የሶሻል

ሚዲያን ጥቅም ካየሁበቸው አንዱ ብዬ ማስበው ይህን የወጌል አገልጋይ ለማውራት እና ስለ አገልግሎቴ ከእርሱ ምክር ለመቀበል እድል ማግኘቴ ነበር። ራቪ ዘካሪያስ ከሆስፒታል አልጋ ላይ ሆኖ ከጻፋቸው የመጨረሻ ጽሑፍች አንዱ የሆነውን "የትንሣኤ አሰላስሎዬ ከሆስፒታል አልጋዬ ላይ" በሚል እንዲህ ያወራናል ሰለሞን አበበ ገብረ መድህን እንደ ተረጎመው ይህን የምጽፈው በቴክሳስ ከሚገኘው የካንሰር ሕክምና መስጫ ሆስፒታል ውስጥ ኾኜ ነው። ከኹለት ወራት በፊት በጀርባዬ ላይ የቀዶ ጥገና ሕክምና ባደረግሁ ጊዜ ሳርኮማ (sarcoma) የሚባል ፥ ዐልፎ ዐልፎ የሚከሠትና አኹን እየታከምሁት ያለ የካንሰር ሕመም ዐይነት እንደተገኘብኝ ሲነገረኝ ደንግጬ ነበር። ለብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር የተባረከና ጤናማ ሕይወት ነበረኝና፥ ይህን ዜና መስማት ማስደንገጡ አይቀረም። ኹል ጊዜም፥ በትንሣኤ መልእክት ኀይል አምናለሁ፤ አኹን ደግሞ ፥የበለጠ አምናለሁ። ከማናቸውም ተስፋዎች ኹሉ የበለጠ ታላቁ መልእክት እርሱ ነው፤ በርግጥም፥ ታላቁ የተስፋ መደላድልም እርሱ ነው።.

በአልጋዬ ላይ ጋደም እንዳልሁ ፍጥረታዊው ዓለም መንፈሳዊ እውነታዎችን ለማስረዳት እንዴት ሊያንጸባርቃቸው እንደሚችል ሳሰላስል ነበር። ካንሰር ማለት ራሱን በእርባና ቢስነት እያራባና እውነተኛ ሕይወት ሰጪ ሕዋሳትን እየተሸቀዳደመ የሰውን ሕይወት በየቀኑ በአንድ እርምጃ ወደ ሞት የሚያስጠጋ ወስላታና ብልሹ ሕዋስ (አፈንጋጭ ሕዋስ) ነው። ይህ ነገር የነፍሳችን ጠላት አዳምና ሔዋንን፥ “በውኑ እግዚአብሔር ተናግሯልን?” በማለት በእግዚአብሔር ላይ ጥያቄ እንዲያነሡ ባደረጋቸው ጊዜ፥ በዘፍጥረት መጽሐፍ የምናነበውንና የውድቀትን ታሪክ ለማገናዘብ የሚያግዝ አስገራሚ ነጸብራቃዊ ተምሳሌት ኾኖ አግኝቸዋለሁ። ቅድመ አያቶቻችን ሕይወት ሰጪ የኾነውን እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ከመምረጥ ይልቅ ያለመታዘዝና የራስን ፈቃድ በራስ የመወሰን ወስላታ ሕዋስ አፈንግጦ እንዲገባባቸውና በሰው ዘር ኹሉ ውስጥ ያለምንም ገደብ እንዲሠራጭ (metastasize) እንዲያደርግ ፈቅደውለታል።.

እንደሚታወቀው፥ እኛ የሰው ልጆች፥ ይኽንን ካንሰር የተባለ ወስላታ ሕዋስ ለመዋጋት፥ በጋራ ኾነን ቢሊየን ዶላሮችን እየከሰከስን በምንፍጨረጨርበት በዚህ ወቅት፥ በዋናነት ኹለት የህክምና አማራጮች ብቻ ከፊታችን ቀርበውልናል ፤ እነርሱም ፥ አስቸጋሪዎቹን አፈንጋጭ ሕዋሳት ለመረፍረፍ የሚሰጠው የጨረራ (radiation) ሕክምና እንዲሁም፥ አሰልቺ ድግግሞሽ የማያጣውና የተቀናጀ ዘዴን የሚጠቀመው ኬሞቴራፒ (chemotherapy) ናቸው።

ወደ ገጽ 10 ዞሯል ....

# ክርስትና በቴህራን ምንን ይመስላል?

በአረባዊቷ ምድር ኢራን በነዋሪዎቿ ላይ የሚደርሰዉ ግፍና መከራ በእጅጉ ከባድ ነዉ። በተለይም ደግሞ በኢየሱስ አምነዉ ከእስልምና ወደ ክርስትና የተለወጡ ኢራናዊያን አማኞች የሚደስርድባቸዉ ስደትና ስቃይ እንዲህ በቃላት ለመግለፅ የሚቻል አይደለም። ምንም አንኳን ምዕራባዊያኑ ሀገሪቱ እያብላላች ባለችዉ ኒዉክለር ትኩረታቸዉን ብትስብም ለዜጎቿ ያላት የሰብአዊ መብት አያያዝ ግን አብሮ የተለወጠ አይደለም።

የኢራናዊያኑ ፕሬዝዳንት ሀሰን ሩሀኒ እንደ አዉሮፓዉያኑ ዘመን አቆጣጠር በ26.01.2016 በዕለተ ማክሰኞ የካቶሊኩን ጳጳስ ፍራንሲስን በቫቲካን በጎበኙበት ወቅት ቢያንስ አንድ እንኳ አጀንዳ በኢራናዊያን የሰብአዊ መብት አያያዝ ዙሪያ ብሎም በዛ ስለሚኖሩ ስለጥቂቶቹ ነገር ግን በብዙ ስቃይ ስለሚኖሩት ክርስቲያኖች ያወሩት ነገር የለም።

ሀገሪቱ ካላት ድምር የህዝብ ቁጥር ዉስጥ 98% በመቶ የሚሆኑት ሙስሊሞች ናቸዉ። ነገር ግን ከቀረዉ 2% ፐርሰንት ምን ያህሉ ክርስቲያን እንደሆኑ የሚታወቅ ነገር የለም። በእርግጥ አንዳንድ ባለስልጣናት የክርስቲያኑን ቁጥር እስከ 90.000 እንደሚደርስ ሲናገሩ በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሰዉ የካቶሊካዉያኑ የተራድኦ ድርጅት ቁጥሩ ከዛ በእጅጉ የበለጠ እንደሚሆን ግምቱን ያስቀምጣል። የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ተቋማት ደግሞ ከ500.000 በላይ የሚሆኑ ክርስቲያኖች ከተለያዩ ቤተ-ዕምነቶች እንዳሉ ይናገራሉ እነዚህም ቤተ-ዕምነቶች ከሚያካትቷቸዉ ዉስጥ ፕሮቴስታንት፣ የኣርመናዉያን ሐዋሪያት፣ካልዲያን እንዲሁም 15.000 የሚሆኑ የሮማ ካቶሊኮች ናቸዉ።

በኢራን ያለዉ ሁኔታ ለየትኛዉም በስመ ክርስትና ለሚጠሩ ቤተ-ዕምነቶች ነገሮች ሁሉ በእጅጉ የሚያስደንቁ ናቸዉ። የኦፕን ዶርስ ሰራተኛ የሆነዉ ማርቆስ ሮዲ እንደሚለዉ ከሆነ “እንደ ቡድንም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ከእስልምና ወደ ክርስትና የተለወጡ ዜጎች በቃላት ለመግለፅ ለሚከብዱ ስቃይና እንግልት ይዳረጋሉ” ይላል።

በዚህች አረባዊት ምድር ላይ ብዙዎች በእስር፣በስቃይና በሞት ፍርሃት ዉስጥ ሆነዉ ይኖራሉ። ሆኖም ግን ኣርመናዉያን፣ካልዲያን አብያተክርስቲያናት ህብረት ለማድረግ በዉስኑ ፍቃድ አላቸዉ ይህም ግን በሐገሪቱ ፖሊሶች ጥብቅ እይታ ዉስጥ ነዉ። በፋርስ ክርስቲያናዊ መፅሐፍትን እና የጽሑፍ ዉጤቶችን ማሰራጨት ብሎም የወንጌል ስርጭት በጥብቅ የተከለከሉ ተግባራት ናቸዉ።

ሮዲ የተባለዉ ግለሰብ ለዶቼቨሌ ሚዲያ በዛ ስላለዉ ሁኔታ እንዲህ ሲል ምስክርነቱን ሰጥቷል “ጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን እንዳትንቀሳቀስ ሆና ተይዛለች። በህብረታቸዉ ፀንተዉ ያሉትም ቢሆኑ መሰባሰባቸዉን በድብቅ ለማድረግ ተገደዋል” ብዙዎቹ ክርስቲያኖች በትናንሽ የቤት ዉስጥ ህብረት ተገድበዉ ቀርተዋል።

## በአደባባይ የሚደረግ የክርስቲያኖች ሰቆቃ

ሮዲ ስለ አንድ ኢራናዊ ክርስቲያን በቴህራን ዉስጥ ስለደረሰበት ነገር ምስክርነቱን ሲሰጥ እንዲህ ይላል “ወደ መንገዱ እየጎተቱ አወጡት እናም አሁን ይህን ዕምነትህን ክደህ ወደ ነበርክበት እስልምና ተመለስ አለበዚያ ትሞታለህ በማለት ሽጉጥ በጭንቅላቱ ላይ በማነጣጠር ያስፈራሩታል” ከዚህ መሰል የአደባባይ ድርጊት በኋላ ወደ እስርቤት ተወስዶ ይጣላል። ይህም አልበቃ ብሎ የእስር ቤቱ ጠባቂዎች የሚያጨሱትን ሲጋራ በተጎሳቆለዉ ሰዉነቱ ላይ በመተርኮስ ያጠፋሉ። የዚህ ሰዉ ዘመዶች ከብዙ ስቃይ በኋላ ከእስር እንዲፈታ ለማድረግ ችለዋል። በአሁኑ ጊዜ ጊዜ ኑሮዉን በጀርመን ሀገር ያደረገ ቢሆንም የደረሰበት መከራ ካሳረፈበት ስጉነት በዛም በጥልቅ ፍርሃት ዉስጥ ሆኖ ይኖራል።



## ከእስልምና ወደ ክርስትና በብዙ እንግልት

ሮዲ እና ማቲያስ እንደሚስማሙት እስልምና እና መካከለኛዉ ምስራቅ ለክርስቲያኖች የመቃብር ስፍራ ነዉ ማለት ይቻላል። ወደ ክርስትና ለመምጣት የወሰኑ ኢራናዉያን የእስር ትዕዛዝ ከዚያም ሲያልፍ ሞት ሊደርስባቸዉ እንደሚችል ያዉቁታል። ብዙዎች ኢራናዉያን ሙስሊሞች ወደ ክርስትና ከመጡም በኋላ ለተወሰነ ጊዜ በዛዉ በእስልምና ይቆያሉ ምክንያቱም ማንም ወደ ክርስቲያኖች የአምልኮ ስፍራዎች መሄድ የተከለከለ ስለሆነ።

“በቤተክርስቲያን የሚደርሰዉ ጫና በእጅጉ ከባድ ነዉ” ሲል ይናገራል ማቲያስ ቮግት የተሰኘዉ ግለሰብ። ኢራን አምባገነናዊ የአንድ ፓርቲ መንግስት ሀገር ስትሆን ህዝቦቿን ከዉጭ ጥቃትና ከእስልምና ባህል ያፈነገጠ ነገር እንዳይኖር በእጅጉ የፖሊስ ቁጥጥር የሚደረግባት ሀገርም ነች።

# ክርስትና በቴህራን ምንን ይመስላል?



**ክርስቲያኖችን ነጻ እናዉጣ!**

የኢራናዊያኑ ፕሬዝዳንት ሀሰን ሩሀኒ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አዉሮፓ ባቀኑበት ወቅት ብዙዎች የብርሃን ተስፋ እንደወጣላቸዉና ሀገራቸዉ ከፖለቲካዊ መገለልና ብሎም ከኢኮኖሚያዊ ጫና እንደሚላቀቁ ተስፋን አድርገዉ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ኢራናዊቷ የዓለም የሰላም የኖቤል ተሸላሚ ሺሪን ኢባዲ አስተያየቷን ስትሰጥ “ሮሃኒ ምንም ሀይልና ስልጣን የለዉም” ሀይል ያለዉ በሀገሪቱ ትልልቅ የሀይማኖት መሪዎች ጋር እንጂ ስትል ትደመጣለች። በኢራን የሼሪያ ሕግ ከፖለቲካዊዉን ህግ በላይ ይሰራል። ምዕራባዉያኑ ከኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ዉጪ አንድም ተፅዕኖ ፈጣሪ ድርድሮች ሊያደርጉ አለመቻላቸዉም በእጅጉ አሳሳቢ ነዉ። ሮዲ እንዲህ ይላል አንድም ሰዉ በግልፅና በጉልህ ክርስቲያኖችን ነፃ እናዉጣ ሲል ሰምቼ አላዉቅም።



**የኒዉክለር ድርድሩ በርን መክፈት አያሳይም**

ምንም ያህል የኢራን እና አሜሪካ ድርድር ቢቀጥል በኢራን ምድር ያለዉን ነበራዊ ሁኔታ ቀያሪ ሊሆን ይችላል? ሮዲም ሆነ ማቲያስ በዛ ያለዉ የሰብዓዊ መብት አያያዝ ይቀየራል ብለዉ እንደማያምኑ ይናገራሉ። ምንም እንኳ በምዕራባዉያኑ ዕምነት ይህ ሁነት ታሪካዊ ለዉጥን ሊያመጣ እንደሚችል ተስፋ ቢያደርጉበትም። ሮዲ እንደሚለዉ ከሆነ ኢራን ዋነኛዉ ትኩረቷ ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ማግኘት ብቻ ነዉ ለዚህም ሲባል ነዉ ይህን የኒዉክለር ድርድር ሴጣናዊ ሀገር ከሚሏት አሜሪካን ጋር ለማድረግ የተቀመጠችዉ። እንጂ ለክርስቲያኑ የሚያስገኘዉ አንድም የተለየ ጥቅም የለም። በአሁኑ ጊዜ ሁለት ክርስቲያን ፓስተሮች ከእስር ተለቀዋል ምንም እንኳ ብዙዎች አሁንም በእስር ላይ ያሉ ቢሆኑም።




ወንጌልን ሳስብ በብዙ እደነቃለሁ የእግዚአብሔር ሃይል ሲገለጥ በብዙ ምስክር ሆኛለውና። ኢራንን ሳስብ አለም ያለወቀውን ትልቅ እውነት ሁሌ አስታውሳለሁ በዚህ ሰአት በአለማችን ወንጌል በፍጥነት ከሚሰፋባቸው እና በየቀኑ ብዙ ሺዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት ከሚቀላቀሉባቸው ምድሮች ፊት አውራሪ ከሆኑት ትመደባለች ። ክርስትና በኢራን በየአማቱ በ19.8% ያድጋል ብዙ መቶ ሺዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት ይጨመራሉ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።


ክርስቶስን የሚወዱ ወንዶች እና ሴቶች በብዙ ጽናት ስለወንጌሉ ዋጋ እየከፈሉ ያሉ ስፍር ቁጥር አይደሉም። ዛሬ በምድረ ኢትዬጵያ ብዙ ነጻነት ክርስቶስን ለማምለክ የታደልን አማኞች ወደ ማዶ አሻግረን እንይ ስለ ወንድሞች እና እህቶቻችን በእግዚአብሔር ፊት እንጸልይ ስለእነርሱ እግዚአብሔርን እናመስግን ።


ትርጉም፡ - ምስጋና ክብረት

**የቀጠለ ....**







ይኹንና ፥ እነዚህ የካንሰር ሕክምና መንገዶች በጨለማ ውስጥ የሞውዜር ቃታን ስቦ እንደመተኮስ ዐይነት ናቸው ፤ ምክንያቱም በሕክምና መንገዶቹ የሚሰነዘሩት ጥቃቶች ፥ አፈንጋጮቹን ሕዋሳት ብቻ ሳይኾን መልካሞቹን ሕዋሶቻችንን ጭምር ይጨረግዷቸዋልና። በመኾኑም ፥ የማታ ማታ ድሉ ቢገኝ እንኳ ፥ ምናልባት ከድል ተነሺው ይልቅ ድል መቺውን ዋጋ ስለሚያስከፍለው ፥ ድሉ “እያነቡ እስክስታ” ዐይነት ድል (pyrrhic) ሊኾን ይችላል።

**ፍጹሙ አምላካችንና መድኀኒታችን**

በእግዚአብሔር ላይ ባመፅን ጊዜ ፥ የመድኅን ፥ ሊያውም የፍጹም መድኅን ፥ አስፈላጊነት በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ የቀረልን ተስፋ ኾነ። ያንፍጹም መድኅንም ፥ ራሱ እግዚአብሔር በገዛ ልጁ አዘጋጀልን። ይኸምነገር ፥ እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ግለሰብ ሕይወት እንዴት ዋጋ እንደሰጠው የሚያመለክት እውነት ነው። ነቢያቱ አስቀድመው እንደተናገሩት ፥ አዳኙ ይመጣል። በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በመሞት ይቀበራል። በአስደናቂው የትንቢት ቃል መሠርትም፥ ኢየሱስ በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሣ ፤ ድል ነሺው በእውነት ድል ነሣ። ሕይወት ሰጪው መንፈስም ተመልሶ ተሰጠን። .

እንግዲህ እኛም  ከሐዋርያው ጋር ይኸን ጥያቄ ማንሣት እንችላለን? “ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ?” (1 ቆሮ. 15፥55)። ኀጢአት በውስጣችን ብልሹው የካንሰር ሕዋስ ነው። ነገር ግን፥ የኢየሱስ ሕይወት፥ ሞትና ትንሣኤው ለእግዚአብሔርን የፍጥረት ሥርዐት በሚጠቅም መንገድ ሞገዱን ቀለበሰው። ስለዚህ፥ ይኽን በዓለትን ሣኤበልባዊ ደስታ እና ክብረው ፤ በሞት መካከልም ሕይወትን እንፈልግ ፤ምክንያቱም መቃብር ድልነሺ አይደለም። አያሸንፍም። ትንሣኤው የውድቀት ኀይል ላይ መልስ የተቀለበሰበትና ታላቁ ፈውስ በማያዳግም ኹኔታ የተሰጠበት ድል ነው። .

የዬሉኒኮላስ ዎል ተስቶፍ፥ ልጁን በከፍታ የመውጣት አደጋ በሞት በተነጠቀ ጊዜ፥ እንዳለው፥ “ሰውን በቅርብ የማጣትን ጣጣ ስልክ በመደወል፥ ክንፍ አልባነትን በአውሮጵላኖች ፥የበጋ አየር ጸባይ የሚያስከትለውን የሙቀት ቃጠሎ በአየር ጸባይ መቈጣጠሪያ ማሽኖች ለመቋቋም አላዳገተንም፤ እነዚህንና ሌሎች ያልተጠቀሱ ጒድለቶችን ለማስወገድና ችግሮቻችንን በሚገባ ለመቋቋም ችለናል ።ነገር ግን፥ ልንመክታቸው የሚገባ ኹለት መሠረታዊ ችግሮች ተደቅነውብን ቀርተዋል፤ እነርሱም በልባችን የሚያድረው እኵይ እና ሞት ናቸው።”

እንግዲያውስ፥ መልሱ ያለው እዚህ ጋ ነው። መልሱ ያለው፥ ሞት የሚወልደውን የዐመፅ ሕዋስን ለማደባየትና ሕያው ሕዋሳትን በእኛ ውስጥ ለማደስ በሚችለው የእግዚአብሔር ልጅ ብርሃን ውስጥ ብቻ ነው። ይህ ምንኛ ውብ እውነት ነው! ምን ዐይነት
የተስፋ መልእክት ነው!

ስለ መስቀሉ እያሰላሰልንና ከሞት የተነሣውን ጌታችንን እያከበርን ባለንበት ጊዜ በመደነቅና በአምልኮተ እግዚአብሔር እንሞላ። በዚህ ወቅት ከተሞቻችን በሞት ሸታ እየታጠኑ ነው። የሕይወት የመዓዛ ሽታ ያስፈልገናል ስሙም ኢየሱስ
ክርስቶስ ይባላል።

ይህ ጽሑፍ በማቲው ፌሮን ለሰንደይ ታይምስ ኦፍ ለንደን ከጻፈው በአማኑኤል ገዛኸኝ የተተኀመ አርትኦት  አማኑኤል ወንድማገኝ እና በሚያዚያ 2 ቀን 2012 ዓ.ም በGospel Coalition ገጽ ላይ ከታተመው በሰለሞን አበበ
ገብረ መድህን በዚህ መልክ ወደ አማርኛ ከተመለሰ ጽሑፍ የተወሰደ ነው ።

# የሚያበራየዉን በሬ አፉን አትሰር!

በኢትዮጲያ የወንጌላዉያን አማኞች ታሪክ ቤተክርስቲያን በብዙ ስደትና መገፋት ዉስጥ ለማደጓ አያሌ ምስክሮች የሚሆኑን ቅሬታዎች በአሁኗ ዘመን ቤተክርስቲያንም ዉስጥ እንዳሉን የሚታወቅ ነዉ። ይህቺ በእዉነተኛ'ኚቱ መሰረት ላይ የተመሰረተችዉ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ጠፋች ስትባል የምትበዛ ፣ የለችም ስትባል እልፍ ህያዋን ሰራዊቶችን የወለደች ቤተክርስቲያንነቷን አሳይታለች። ወንጌል በባህሪዉ በድሎትና በብዙ ተድላ ከማደግ ይልቅ በብዙ መገፋትና ጭንቅ ዉስጥ እንደ ሰደድ እሳት የሚቀጣጠል መሆኑን ጠንቅቀን እንረዳለን ሆኖም ግን ከሰሞኑን በሰማንዉ በዚህ የወንጌል ስራ ዉስጥ ፊት-አዉራሪ በመሆን በማገልገል ላይ ያሉ የመንግስቱ ወንጌል ሰራተኞች (የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች) በከፍተኛ የኢኮኖሚ ድቀት ሳቢያ በብዙ ችግር ከነቤተሰባቸዉ ችግር ላይ መዉደቃቸዉን ሰምተናል። እንደዚህ እንደዛሬዉ ባሉ ሰዉ አመጣሽ ችግሮች ቤተክርስቲያን ህልዉናዋ ፈተና ላይ በሚወድቅበት ጊዜ በከፍተኛ ርብርብ ለመጣዉ ችግር ተገቢዉን ምላሽ መስጠት የዉዴታ ግዴታ እንደሆነ መመሪያችን የእግዚአብሔር ቃል በግልፅ ይደነግጋል። በ1ቆሮንቶስ 8፡ 9-11 “9፡ ሕግስ ደግሞ ያን አይልምን? የሚያበራየዉን በሬ አፉን አትሰር ተብሎ በሙሴ ሕግ ተጽፎአልና። እግዚአብሔርስ ስለ በሬዎች ይገደዋልን? 10፡ ይህን የሚለዉ ፈጽሞ ስለ እኛ አይደለምን? የሚያርስ በተስፋ ሊያርስ የሚያበራይም እንዲካፈል በተስፋ ሊያበራይ ስለሚገባዉ በእዉነት ስለ እኛ ተጽፎአል። 11፡ እኛ መንፈሳዊን ነገር የዘራንላችሁ ከሆንን የእናንተን የሥጋዊ ነገር እኛ ብናጭድ ትልቅ ነገር ነዉን?” በማለት ሐዋሪያዉ ቅዱስ ጳዉሎስ በመልዕክቱ ያሳስባል። ከእነዚህ የመንግስቱ ሰራተኞች በጸጋቸዉ ተጠቅመን በጸሎታቸዉ ተባርከን ዛሬ እንዲህ ባለ ሁኔታ ለእነርሱ በጉድለታቸዉ አለመቆም ከጌታም ዘንድ የሚያስጠይቅ ጥፋት ይሆንብናል። እናም ሁሉም አማኞች ላሉበት አጥቢያ የሚጠበቅባቸዉን ሁሉ እንዲያደርጉና አሁን በተቋቋመዉ የእርዳታ አስተባባሪ ኮሚቴ በኩል ደግሞ የእነዚህ ሰዎች ጉድለት እናንተ ሙላታቸዉ በመሆን የበኩላችሁን እንድታደርጉና ከታሪክ ተወቃሽነት እንዳን ስል ከታላቅ ወንድማዊ አክብሮት መልዕክቴ እነሆ። ሰምታችሁ ምላሽ ስለምትሰጡ ሁሉ ክብረት ይስጥልኝ እላለሁ!

የተቸገሩ አገልጋዮችን እና የአገልጋይ ቤተሰቦችን ለመደገፍ በካዉንስሉ የተከፈተዉ የሂሳብ ቁጥር

- ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ ፦ 26000100018241
- ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ ፦ 1019601001873

ምስጋና ክብረት
የሊደርሺፕ ተማሪ፣ የሚሽን ሞብላይዘር እና የወንጌል ሰባኪ

# የጸሎት ጥሪ ለሶማሌ የህዝብ ክፍል

| | |
|---|---|
| የህዝብ ክፍል መጠሪያ ሰም፦ | ሶማሊ |
| አለምአቀፍ የህዝብ ቁጥር ፦ | 23,131,000 |
| በአለም ላይ የሚገኙበት አገራትቁጥር፦ | 24 |
| የህዝብ ቁጥር፦ | 7,097,000 |
| ዋና ቋንቋ፦ | ሶማልኛ |
| የህዝቡ ዋነኛ ሀይማኖት፦ | እስልምና (99.86%) |
| ክርስትያን፦ | 0.14% |
| ኢቫንጀሊካል፦ | 0.03% |
| በቋንቋቻውየተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱስ (የኦድዮ መጽሐፍ ቅዱስ) ፦ | የተሟላ |
| የቤተክርስትያን ተካዮች፦ | በህዝቡ መካከል ይገኛሉ |

## መግቢያ

በሰሜን ምስራቅ የአፍሪካ ክፍል በተለምዶ የአፍሪካ ቀንድ” ተብሎ በሚታወቀዉ እና በመካከለኛው ምስራቅ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሶማሊዎች በስምንት አገራት ውስጥ ተበታትነው ይገኛሉ። በአፍሪካ አህጉር ውስጥ ወጥና በጣም ተመሳሳይ ከሆኑት የህዝብ ክፍሎች አንዱ ናቸው። ስድስት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን ምእራብ ሶማሊያ በመባል ይታወቃሉ።

ሶማሊዎች አንድ የጋራ ቋንቋን የሚጋሩ፣ አንድ የጠበቀ እምነት ተከታዮች እና የዘላን አይነት የአኗኗር ዘይቤአቸውን እንደ አንድ ባህላዊ ቅርስን አካል ያደረጉ ናቸው። ስማቸው የተገኘው “ሶማል” ከሚሉት ቃላት ሲሆን ቃል በቃል ትርጉሙም “የአውሬን ወተት ወተህ ለራስህ አለብ!” ማለት ነው።ለሶማሊዎች ይህ በእውነቱ ምቾት አልባ የሆነ የእንግዳ ተቀባይነት መንገድ መግለጫ ነው። ሶማሌዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ያሉት በአፍሪካ ቀንድ በ1200ዓ.ም ከክርስቶስ ልደት በኀላ ነው። ከዚያም ወደ ምዕራብና ደቡብ ለሚቀጥሉጥ 150 አመት መስፋፋትጀመሩ። የእስልምና ሀይማኖትን የተቀበሉት በ 1550ዓ.ም ሲሆን ይህም ዛሬ ሱማሊያ ብለን በምንጠራው የባህር ዳሮች ላይ ለንግድ ልውውጥ የሠፈሩ የአረብ ነጋዴዎች አስተዋፅዎ ነው። እ.ኤ.አ.በ1650 ወደ ኢትዮጵያ ተዘዋወሩ።

## አኗኗራቸው ምን ይመስላል?

የሶማሊያ ማህበረሰብ ባል፣ ሚስት እና ልጆች ባካተተ ጥብቅ ቤተሰብ ላይ የተመሠረተ ነው። አንድ ቤተሰብ የበጎች ወይም የፍየሎች መንጋ እንዲሁም ጥቂት ግመሎች አሉት።አንዳንዶች ደግሞ ወተት ለማግኘት ግመሎች ሊኖሯቸው ይችላል። አንድ ሰው ያሉት የግመሎች ቁጥር በበዛ ልክ ክብሩም ከፍ ይላል።

ሶማሊያውያን ራሳቸውን እንደ ተዋጊዎች ይቆጥራሉ። ወንዶቹ ይበልጥ ውጤታማ ተዋጊዎች እንዲሆኑ እራሳቸውን ለማሠልጠን ብዙውን ጊዜ የመንጋዎቹን ኃላፊነት ለሴቶቹ ይተዋሉ። በጣም ግለኛ እና በጎሳዎች የተከፋፈሉም ናቸው። ብዙውን ጊዜ በጎሳዎች መካከል ጦርነቶች የሚከሰቱ ሲሆን በዚህም ምክንያት ብዙ ሰዎች ለሞት ይዳርጋሉ።

አራት ዋና የሶማሌ የጎሳ ቡድኖች አሉ። ሁለቱ ትልቅ ጎሳዎች ሶማል እና ሳብ ናቸው።ሶማሎች በዋነኛነት ዘላን እረኞች ናቸው። ሳቦች ደግሞ ብዙውን ጊዜ በማኅበረሰቡ ውስጥ እንደ ገበሬ ወይም የእጅ ሙያተኛ ሰፍሮ የሚኖሩ ናቸው።

ዘላኖች የሚኖሩት ከሣርና ጭቃ በተሸፈኑ፣ ከእንጨት ቅርንጫፎች በተሠሩ በተንቀሳቃሽ ጎጆዎች ውስጥ ነው። ቤቶቹ በቀላሉ ተነቃቅለው እንስሳት ላይ ተጭነው ከእንስሶቹ ጋር እንዲንቀሳቀሱ የሚችሉ ናቸው።ይበልጥ የተቋቋሙት የሶማሌ ገበሬዎች ከስድስት እስከ ዘጠኝ ጫማ ከፍታ ባላቸው ክብና ቋሚ ጎጆዎች ውስጥ ይኖራሉ። ምግባቸው ወተት፣ ሥጋ እና የዱር ፍራፍሬዎችን ያጠቃልላል። የበለጠ የተለያዩ ምግቦችን የሚያካትት የአመጋገብ ስርዓት አላቸው የበቆሎ፣ ባቄላ፣ ሩዝ፣ እንቁላል፣ ሙዝ፣ ቴምር፣ማንጎ እና ከሚጠጣ ደግሞ ሻይን ያጠቃልላል።

የተትረፈረፈ የምግብ አቅርቦት መኖሩ በጎሳዎች መካከል የጀረዳ ምልክት ነው። እያንዳንዱ ቤተሰብ ለዘመዶቻቸው እና ለወዳጆቻቸው ድግሶችን ያዘጋጃሉ። የአንድ ቤተሰብ ትልቅነት የሚለካው በድግሶቹ ድግግሞሽ፣ በተጋበዙ ሰዎች ብዛት፣ በሚቀርበው ምግብ ጥራት እና ብዛት ነው።

በተለምዶ ሶማሊያ እንደ ቶጋዎች (የሮማውያን የወንዶች ካባ) አይነት በቀላሉ የሚለበሱ ደማማቅ ቀለም ያላቸው ልብሶችን ይለብሳሉ። ወንዶቹም ሸርጦችን ይለብሳሉ።

## እምነታቸው ምንድን ነው?

ምንም እንኳን ሶማሊዎች በአብዛኛው የሻፋይት ሙስሊሞች ቢሆኑም፣ በርካታ እምነቶች እና ልምዶች ከእስልምና ልምዶቻቸው ጋር ተቀላቅለዋል። መደበኛ የእስልምና ጸሎቶች ብዙውን ጊዜ መንደርተኞች፣ የከተማ ነዋሪዎች በረከቶችን፣ ውበትን እና በዓለም ጉዳዮች ላይ ምክሮችን ለማግኘት ወደ ዋዳአድ የመንደሩ (የሃይማኖት ሊቅ) አዘውትረው ይሄዳሉ።

## ፍላጎቶቻቸው ምንድን ናቸው?


ትምህርት ቤት የሚማሩ የሶማሊ ሕፃናት በጣም ጥቂት ናቸው፣ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አዋቂዎች ደግሞ ማንበብና መጻፍ አይችሉም። እስከ 1972 ዓ.ም ድረስ የተጻፈ ጽሑፍ ስላልነበራቸው ይህ ብዙ ላያስደንቅ ይችላል።

የዘመናዊ የጤና አገልግሎቶች ተደራሽነት በኢትዮጵያ በጣም አነስተኛ ነው። ድርቅ፣ ረሃብ እና ጦርነቶች በርካታ ችግሮችን ፈጥረዋል። ከ1970 ጀምሮ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት በሺዎች የሚቆጠሩ ሶማሊያዎችን ለሞት ዳርጓል።

ትርጉም ፡ ኪሩቤል ጎበና ( ሚሽን ሞብላይዘር)
ምንጭ ፡ ጆሽዋ ፕሮጀክት
አርትኦት ፡ አማኑኤል ወንድማገኝ

## ለሶማሌ ህዝብ ክፍል የጸሎት ርዕሶች

- በጸሎት እና በምልጃ ወደ ሶማሌ ህዝብ ሚሄዱ እንዲበዙ ምድሪቱ ለወንጌል እንድትከፈት፣ የሚተጉ የጸሎትቡ ድኖችን እንዲያስነሳ ጸልዩ ።
- በሶማሊያ ላይ ትኩረት ለሚያደርጉ የተልዕኮ አገልግሎቶች ሞገስ እና ጥበብን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ጠይቁ።
- የኢየሱስ ፊልም በማሳየት የሚሰራው የወንጌል አገልግሎት በህዝቡ መካከል ውጤታማ እንዲሆን ጸልዩ።
- ወንጌል ወደዚህ ህዝብ በቴሌቪዥን እና በጌዲዬ በሚሄድበት ወቅት ውጤታማ እንዲሆን አብዝታችሁ ጸልዩ ።
- ህብቡ ወንጌሉን ለመቀበል ስለ ክርስቲያኖች ያለውን አመለካከት እና ልብ እግዚአብሔር እንዲቀይር እንጸልይ
- በህዝቡ መካከል እነርሱን የምትመስል ጠንካራ ቤተክርስቲያን እንድትተከል እንጸልይ








# የተልዕኮው መዘውር፡ ጆሽዋ ፕሮጀክት

የጆሽዋ ፕሮጀክ ጥቂት  የክርስቶስ ተከታዮች ወይም ምንም ተከታዬች  ያሉባቸውን  የአለማችን  የህዝብ  ክፍሎች ለማሳየት እና የተልዕኮ ስራዉን በመረጃ ለመደገፍ  የተዘጋጀ ፕሮጀክት (ጥናት)  ነው። ትክክለኛና በየጊዜው የሚሻሻል የህዝብ ክፍሎች መረጃ ታላቁን ተልዕኮ ለመፈፀምና ለመጨረስ ወሳኝ ነው። በመጨረሻው ቀን በእግዚአብሔር ዙፋኑ ፊት ከነገድ፣ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስ ለብሰው የዘንባባን ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑ እና በበጉ ፊት እንደሚቆሙ በታላቅም ድምጽ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ምስጋና እንደሚያቀርቡ እንደሚሰግዱ  ራዕይ 5፡9 እና ራዕይ 7፡9-10 ይነግረናል።  ጆሽዋ ፕሮጀክት ከታላቁን ተልዕኮ አጀንዳ ሰዎችን ከየህዝብ ክፍሎች እና ነገዶች  ደቀ መዝሙር የማድረግ የቤት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይሰራል

Ø በዓለማችን ያሉ የህዝብ ክፍሎች እነማን ቻቸው?

Ø  የትኛዎቹ የህዝብ ክፍሎች ገና በመካካለቸው የቤተክርስቲያን መተከልን ይጠብቃሉ?

Ø  ያልተደረሱትን እና በጥቂቱ የተደረሱትን ለመድረስ ምን አይነት የአገልግሎት ግብዐቶች አሉ?

ጆሽዋ ፕሮጀክት በሁሉም ህዝብ ክፍሎች ፈርቀዳጅ የሆኑ የቤተክስቲያን ተከላ እንቅስቃሴዎችን ለማበረታታት፣ የተልዕኮ አገልሎቶችን ውጤታማ የማስተባበር ጥረትን ምቹ ለማድረግ የህዝብ ክፍል መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል እንዲሁም ያዳርሳል ። ጆሽዋ ፕሮጀክት አያሌ የሆኑ የተልዕኮ ጥናት አድራጊዎችን ስራ በማጠናከር በተቻለ መጠን የተሟላ የሁሉንም ህዝብ ክፍሎች ዝርዝር ያዘጋጃል። በስራው ሂደት የመረጃ ስህተቶች፣ ድግግሞሽ እና መደራረብ ሊኖር ይችላልና መረጃዎቻችን ያለማቋረጥ ይሻሻላሉ አስተያየቶችንም እንቀበላለን።

ያልተደረሱ ወይም በጥቂት የተደረሱ የህዝብ ክፍሎች የሚለውን የመለየት ስራ የሚሰራው በአንድ ህዝብ ውስጥ ከአጠቃላይ የህዝብ ቁጥር ከመቶ ሁለት ፐርሰት ወንጌል አማኝ መኞር እና የአጠቃለይ የስላሴ አማኚያን ወይም የክርስትና ክፍል አምስት ፐርሰንት መኞር አለመኞር ነው። ይህ ማለት በቀላሉ አንድ ህዝብ ከ2 % በታች የወንጌል አማኞች እና 5% በታች የክርስትና አማኝ ማህበረሰብ ሲኖረው በወንጌል ያልተደረሰ ወይም በጥቂቱ የተደረሰ የህዝብ ክፍል ብለን እንጠራዋለን። ይህ የጥናት ዝርዝር ያላለቀው የታላቁ ተልዕኮ ስራዎች ላይ ለማተኮር ይረዳል። ምኞታችን ይህን ዝርዝር የተልዕኮ አገልግሎቶች፣ ቤተዕምነቶች ፤ ቤተክርስቲያኖች እና ሚሲዮናዊያን በእያንዳንዱ ባልተደረሱ እና በጠቂቱ በተደረሱ የህዝብ ክፍሎች መካከል ወንጌል በከፍተኛ ፍጥነት እና ትጋት ለማድረስ እንዲጠቀሙበት ነው። እንዲሁም ጆሽዋ ፕሮጀክት የወንጌል መደረስን ሒደቶች የሚያሳዩ መለኪያዎችን ያስቀመጠ ሲሆን በሆነ ግዜ ብቅ እያሉ የሚጠፉ መረጃዎችን ላይ ተመረኩዞ የሚሰራም አይደለም።

<u>ታሪክ እና ፕሮጀክቱ ያለበት ደረጃ</u>

የጆሽዋ ፕሮጀክት በ1995 የኤዲ 2000 (AD2000) እና ቢዮንድ ሙቭመንት (Beyond Movement) አካል ሆኖ ተጀመረ። ከ2001 እስከ 2005 እ.አ.አ በተለያዩ ጊዜያት (ከካሌብ) ፕሮጀክት፤ አይ ሲ ቲ ኤ፤ ዎርልድ ሀልፕ (cawb project ፡ ICTA and World Help) ጋር መደበኛ እና ቀጥተኛ  ባልሆነ መንገድ አብሮ ሲሰራ ቆይቷል። ከ2006 ዓ.ም እ.አ.አ ጀምሮም  የፍሮነትር ቬንቸርስ (Frontier Ventures) በቀድሞ ስሙ ዩኤስ ሴንተር ፎር ዘ ዎርልድ ሚንስተሪ (U.S center for world mission Ministry) አገልግሎት አካል ሆኖአል። ጆሽዋ ፕሮጀክት ያልተደረሱትን ህዝብ ክፍሎች አጉልቶ በማሳየት የታላቁን ተልዕኮ ያላለቁ ስራዎችን በማብራራት ያግዛል።

ዋናው የጆሽዋ ዝርዝር በአለም አቀፍና (በህብረት ድርጅቶች ) ተቀባይነት የነበረው ትልልቅ ያልተደረሱ (ህዝቦች-ቋንቋዎች) ህዝብ ክፍል እና ተዛማጅ የአገልግሎት እንቅስቃሴዎች መረጃ ዝርዝር ነበር። የጆሽዋ ፕሮጀክት ዝርዝር በብዛት ያልተደረሱ ሰዎች መሀል ፈርቀዳጅ የቤተክርስቲያን ተከላ ንቅናቄ ሒደት በግልፅ ለማቅረብ ሞክሯል።

ይህ ፐሮጀክት ከዚያም በኃላ ይህን ዝርዝር ወደ ሁሉም ወዳልተደረሱ እና በጥቂቱ ወደ ተደረሱ የህዝብ ክፍሎች በማስፋፋት ከቋንቋ- ህዝብ መስተጋብር ባለፈ ወደ ህዝብ ክሎች ጥናት አድጓል።

ይህ የጆሹዋ ፕሮጀክት በድህረገጽ፣ በሞባይ መተግበሪያ ( አፕሊኬሽን) እና በተለያየ መልኩ ያለ ሲሆን አማኞች የቀረውን
የታላቁን ተልዕኮ የቤት ስራ የት ጋር እንዳለ እያዩ እንዲጸልዩ፣ ሚሲዬናውያንን እንዲሊኩ እና ሚሲዬናዊያን እየሆኑ እንዲሄዱ ት፤ልቅ ግብአት ነው ። ግብዣዬ ቢያንስ በቀን ለ 5 ደቂቃ በወንጌል ላልተደረሱ ህዝቦች እንድንጸልይ ነው።

በዚህ ሊንክ https://joshuaproject.net/  ድህረ ገጹን ይጎብኙ

ትርጉም ፡ ህልዳና ብሩክ

ጽሑፍ ፡ ረድኤት ብርሃኑ

አርትኦት፡ አማኑኤል ወንድማገኝ

ምንጭ፡ ጆሹዋ ፕሮጀክት